**ወድ አንባቢ ሆይ!**

አንዳንድ ጊዜ ስለ ሰዉ ሕይወት ምንነት ጥያቄ ተፈጥሮብዎ ያወቃል? ለምን ዓላማ እንደተወለዳና እንዴት ደስተኛ መሆን እንደሚቹሉ ጥያቄ ሊኖርዎ ይችላል፡፡ ይህ ከሆን እነ ዚህ ትምህርቶች በጣም ይረዳዎታል፡፡

**ክፍለ ትምህርቶች**

1. በዓለም እየሆነ ያለዉ ምንድን ነዉ?
2. ስለ እግዚአብሔር እዉነቱ ምንድን ነዉ?
3. ሕይወት ምንድን ነዉ?
4. የሕይወትን ዋና ፍላጎት እንዴት ማሟላት ይቻላል?
5.. ከሞት በኋላ ምን አለ?
6 እዉነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?

የመጀመሪያዉ ክፍለ ትምህርት በራሱ ሙሉ የሆነ ሲሆን ለሌሎች ትምህርቶችም እንደመግቢያነት ይረዳል፡፡ እነ ዚህ ትምህርቶች እያንዳዱ ሰዉ ስለ ሕይዎት ያሉትን ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

እያንዳዱ ትምህርት የተዘጋጀዉ የመልዕክቱን ይዘት በማነባ መረዳት እንዲያስችልዎ ተደርጎ ነዉ፡፡ በቃል የሚያዙት ጥቅሶችና የመልመጃ ጥያቄዎች የዚህ ዝግጅት አስፈላጊ ክፍሎች ናቸዉ፡፡ በእያንዳዱ ክፍለ ትምህርት ዉስጥ የማገኙትን የቃል ጥቅሶች ጊዜ ወስደዉ ያጥኗቸዉ፡፡ እንዲሁም የመልመጃ ጥያቄዎችን ይመልሱ ፡፡

እያንዳንዱን ክፍለ ትምህርት ሲያጠናቅቁ በዚህ መጽሐፉ መጨረሻ ላይ ለማገኙት ጥያቄዎች መልሳቸዉን ይስጡ፡ እያንዳንዱን ክፍለ ትምህርት በሚያጠናቅቁበት ጊዜ ሁሉ ይህን ያድርጉ፡፡ ስደስቱን ክፍለ ትምህርቶች ካጠናቀቁና ለእያንዳዱ ክፍለ ትምህርት ጥያቄዎች መልሶችን ሰጥተዉ ካጠናቀቁ በኋላ የሰጡአቸዉን መልሶች በመፅሐፉ በስተጀርባ በተገለፀዉ አድራሻችን ወይም በአቅራቢያዎ ወደ ማገኘዉ የግሎባል ዩኒቨርሲቲ ጽሕፈት ይላኩ፡ ትምህርቱን እንዳጠናቀቁ የምስክር ወረቀት በአድራሻዎ እንልክልዎታለን፡፡

መማመት እንደሚቹሉት ለሕይወት ዓበይት ጥያቄዎች መልስ ማገኘት የግል ጥረትን የሚጠይቅ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ እነ ዚህ ትምህርቶች ግልጽ በሆነ መንገድ ስለቀረቡ በቀላሉ ለረዳኣቸዉ የሚቹሉ ናቸዉ፡፡ ይህን ትምህርት በሚያጠኑበት ጊዜ ሁሉ ወደ አዕምሮዎ የሚመጡ ሌሎች ጥያቄዎችን ይፃፏቸዠ፡ ለጥያቄዎችዎ መልስ ለማገኘት ተጨማሪ እርዳታን ከፈለጉ ወይም አስተያየት ካለዎ ይፃፉልን፡፡

*እግዚአብሔር ይባርክዎ!*

ዳሬክተር

# 1. በዓለም እየሆነ ያለዉ ምንድን ነዉ?

## በዚህ ትምህርት የሚያጠኗቸዉ

እዉነትን ማወቅ የሚቹሉት እንዴት ነዉ?

ዓለም እንዴት ተጀመረች?

ዓለም የገጠማት ብልሽት ምንድን ነዉ?

ዓለም ምን ተስፋ አላት?

## ክፍል 1

**እዉነትን ማወቅ የሚቹሉት እንዴት ነዉ?**

**ከሳይንስ፣ ታሪክ እና የህይወት ልምምድ**

ስለዓለም እና በወስጧ ስለሚኖሩ ሕዝቦች ከሳይንስ፣ ከታሪክ፣ እና ከሞየት ብዙ ድንቅ ነገሮችን መማር ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ለአብዛኞቹ አበይት ጥያቄዎች መልሳቸወን ከእነዚህ ምንጮች ማግኘት አይችሉም፡፡ ሕይወት እንዴት እንደተጀመረ፣ ዓላማው ምን እንደሆነ እና ወደፊት ምን እንደሚጠብቀዉ አይናገሩም፡፡

ከመጽሐፍ <u>ቅዱስ</u>

ዓለም ለምን እና እንዴት እንደሰራች በትክክል ሊነግርዎ የሚችል ሰሪው ብቻ ነው፡፡ እርሱ በመጽሐፍ ቅዱሱ ወስጥ ስለእነዚህ እወነታዎች ይነግረናል፡፡ በዚህ ዓለም ለመኖር የሚያስችለንን ትክክለኛ መመሪያ የሚሰጥ መጽሐፍ ነው፡፡

**ይህ የሕይወት ዓበትይ ጥያቄዎች ኮርስ**

እነዚህ ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎችዎ መልስ ከሚሆኑት በርካታ ጥቅሶች መካከል ጥቂቶቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳሉ፡፡ ከእያንዳንዱ ጥቅስ በፊት የሚገኝበት ምዕራፍና ቁጥር ይጠቀሳል፡፡ ይህም የመጽሐፉን ስም፣ ምዕራፍ እና ቃሉ የሚገኝበትን ቁጥር የሚያካትት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከተጻፈባቸው ቋንቋዎች ወደተለያዩ ቋንቋዎች ስለተተረጎመ ብዙ ትርጉሞች አሉ፡፡ እዚህ ላይ የሚጠቀሱት የእግዚአብሔር ቃሎች እርስዎ ካሉዎት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር ትንሽ የተለዩ ወይም አንድ አይነት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እዚህ ላይ የተጠቀሱት ከቀደሞው ትርጉም /1962/ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እና በ1993 ዓ.ም ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡

# ክፍል 2

## ዓለም እንዴት ተጀመረች?

### እንዲሁ ተገኘች?

ዓለም ከየት መጣች? እንዲሁ ተገኘች ወይስ ታላቅ አዕምሮ ዕቅድት በታላቅ ኃይሉ ሰራት ብለዉ ራስዎን ጠይቀዉ ያወቃሉ (

መኪና ወይም አወሮፕላን በሚያዩበት ጊዜ እንዲሁ እንዳልተገኙ ያወቃሉ፡፡ በተወሰነ የአሰራር ዘዴ እንዲንቀሳቀሱ አደርጎ ያቀደ እና የሰራቸው ሰው አለ፡፡

## ዓለም የተፈጠረችዉ በዕቅድ ነዉ

ዓለም እና በወስጧ ያሉ ነገሮች በሙሉ እየሰሩ ያሉት በአንድ የተወሰነ ስርዓት ሲሆን ይህንም የተፈጥሮ ህግ ብለን እንጠራዋለን፡፡ ሳይንስ ስለእነዚህ የተፈጥሮ ህጎች ብዙ ግኝት ባደረገ ቁጥር አጠቃላዩን ፍጥረተ ዓለም በዕቅዱ መሰረት ፈጥሮ በስርዓት የሚያስኬድ እና የሚጠብቀው አንድ አካል እንዳለ እናወቃለን፡፡ እርሱም ሁሉን ቻይ እና ሁሉን አዋቂ የሆነው ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው፡፡ እርሱ ጌታ እና የፍጥረት ሁሉ ገዢ ነው፡፡

**እነዚህን ጥቅሶች በቃልዎ ይያዙ**

ዘፍ1፡ 1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፡፡

የሐ1፡ 3 ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፡፡

## እግዚአብሔር የፈጠረዉ ፍጹም የሆነችን ዓለም ነዉ፡፡

እግዚአብሔር ጻሐይን፣ ጨረቃን፣ ከዋክብትን እና መሬትን ፈጠረ፡፡ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር እንዳይጋጩ ምህዋር አበጀላቸው፡፡ በመሬት እና በጻሐይ መካከል ያለው ዕርቀት በጣም ተቀራርበው ሁሉም ነገር እንዳይቃጠል ወይም ደግሞ በጣም ተራርቀው ሁሉም ነገር በረዶ እንዳይሆን በትክክለኛ ዕርቀት ላይ አስቀመጣቸው፡፡ ወቅያኖስ እና የብስ ፍጹም የሆነ ተመጣጣኝነት ያላቸው እና ከባቢ አየሩም ትክክለኛ ነበር፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ፈጠረ፡፡ ከሁሉም በመጨረሻ ሰውን ፈጥሮ ውብ እና ድንቅ በሆነች ዓለም ወስጥ አስቀመጠው፡፡

ይህን ቁጥር በቃልዎ ይያዙ

ዘፍ 1፡ 31 እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበር፡፡

## እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረበት ምክንያት

እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረ በፍጥረቱ ደስ ለመሰኘት ነው፡፡ ሰዎችን የፈጠረው ደግሞ ልጆቹ እንዲሆኑ፣ እንዲወዳቸው እና በእነርሱ ደስ እንዲለው ነው፡፡ ምድርን የሰራት ለእነርሱ መኖሪያነት ነው፡፡ እግዚአብሔር የፍጥረተ ዓለሙን ውበት እና ስርዓት እያየ መደሰት ይችላል ነገር ግን ከሁሉም በላይ የሚያስደስተው ነገር ለልጆቹ ያለው ፍቅር ነው፡፡

ራዕይ 4፡ 11 አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፣ በፈቃደህም ተፈጥረዋልና ሆነዋልምና፡፡

መዝ 149፡ 4 እግዚአብሔር በሕዝቡ ደስ ይለዋልና፡፡

እግዚአብሔር ልጆቹ እንደእርሱ እንዲሆኑና ከስራው ተካፋይ እንዲሆኑ ፍላጎቱ ነበር፡፡ ስለሆነም ለመጀመሪያው ወንድ አዳም እና ለመጀመሪያዋ ሴት ሔዋን በብዙ መልኩ ከራሱ ጋር የሚቀራረብ ባህሪ ሰጣቸው፡፡ እግዚአብሔር ያስተምራቸው ነበር፡፡ በእርሱ ዕርዳታ ሰው ምድርን መግዛት ይችል ነበር፡፡

ዘፍጥረት 1፡ 26 «እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን በአምሳላችን እንስራ . . . በምድር ሁሉ ላይ ስልጣን ይኑራቸው፡፡»

### ይህን ይስሩ

- ዓለም ለምን እና እንዴት እንደተሰራች የሚነግረን መጽሐፍ የቱ ነው?
- የተፈጥሮ ህግ ብለን የምንጠራቸውን የፍጥረተ ዓለም ስርዓቶች የመሰረተው ማነ ነው?
- ዓለም የተፈጠረችው ለማነ ደስታ ነው?
- ዓለም መጥፎ ነበረች ወይስ መልካም ?
- እግዚአብሔር ለዓዳምና ሔዋን የሰጣቸው ባህሪ እንደማነ ነበር?
- የእግዚአብሔር ፍላጎት ሰዎች በፍቅሩ እንዲረኩ እና የእርሱ__________እንዲሆኑ ነበር፡፡

በ __________ እርዳታ ሰው በ __________ላይ ስልጣነ እንዲኖረው ታቅዶለት

ነበር፡፡

*ያጡትን ክፍል ወደኋላ ተመልሰዉ በማየት መልሶችዎን ያመሳክሩ፡፡ በትክክል ያልመለሱት ካለ ያስተካክሉት፡፡*

# ክፍል 3

## ዓለም የገጠማት ብልሽት ምንድን ነው?

### አንድ ስህተት ተፈጠረ

ዙሪያዎን ሲመለከቱ መከራን፣ ሐዘንን፣ ጠበን፣ አመጽን፣ ጦርነትን፣ ረሐብን፣ እና ሞትን ያያሉ፡፡ ዓለም አሁን ፍጹም አይደለችም፡ የተፈጸመው ስህተት ምን ነበር፡፡ ይህች በአንድ ወቅት ፍጹም የነበረችዋ ዓለም በእግዚአብሔር ጠላት እና በራሱ በሰው ተበከለች፡፡

### የእግዚአብሔር ጠላት

እግዚአብሔር ሰይጣን ወይም ዲያቢሎስ የሚባል ጠላት አለው፡ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነበር፡፡ ነገር ግን ትዕቢተኛ እና አመጸኛ ሆነ፡፡ አሁን ሰይጣኑ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ይቃወማል፡፡ እግዚአብሔር ሊረዳን ይፈልጋል፣ ሰይጣን ሊያጠፋን ይጥራል፡፡ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ባለው ፍቅር እና ህብረት ሊደሰት ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን ዲያቢሎስ ከእግዚአብሔር ሊለየን ይጥራል፡፡ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ይልቅ ዕርሱን እንድንከተለው ለማድረግ ጥረት ያደርጋል፡፡

### የሰው ሐጢአት

ሰይጣን ለአዳም እና ሐዋን ስለእግዚአብሔር ወሸት ነገራቸው፡ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዲያደርጉ ማለትም እንዳይታዘዙ አሳመናቸው፡ ሰወን ከእግዚአብሔር ስለሚለይ ኃጢአት ሞትን እንደሚያመጣ እግዚአብሔር አዳምን አስጠንቅቆት ነበር፡፡ ሕይወት የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው፡ ስለዚህ ከእርሱ መለየት ፍጻሜው ሞት ነው፡ አዳም እና ሐዋን ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰይጣንን ለማመን መረጡ፣ የእግዚአብሔርን ህግጋት ጥሰው የራሳቸውን መንገድ በመከተል ለዓለም ሁሉ አስከፊ ጥፋትን አመጡ፣

### የኃጢአት ወጤቶች

ኃጢአት በዓለም ላይ በሽታን እና ሞትን አስከትሏል፡፡

**ሮሜ** 5፡ 12 «ስለዚህ ኃጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደገባ ሁሉ፣ ሞትም በኃጢአት በኩል ገብቶአል፡ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፣ ምክንያቱም ሁሉም ኃጢአትን ሰርተዋል፡፡ »

ኃጢአት በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል የነበረውን ህብረት አበላሸው፡፡ ሰው ዓመጸኛ የሚዩታዘዝ እና ኃጢአተኛ እስከሆነ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ሊኖረው አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑ ቀርቶ የኃጢአት አገልጋይ ይሆናል፡፡

**ሮሜ** 6፡ 16 ራሳችሁን እንደ ባሪያ አድርጋችሁ ስታቀርቡ ለምትታዘዙት ለእርሱ ይኸውም ወደ ሞት ለሚወስደው ለኃጢአት ወይም ወደ ጽድቅ ለሚያደርሰው ለመታዘዝ ባሮች እንደሆናችሁ አታውቁምን?

እግዚአብሔርን ባለመታዘዛችን ከሰይጣን ዓመጽ ጋር ተባብረን አገዛዙን መቀበላችን ነው፡፡ ምድር እግዚአብሔር እና ሰይጣን የሚዋጉባት የጦር ሜዳ ሆናለች፡፡ ከየትኛው ወገን እንደሚሆኑ መምረጥ አለብዎ፡፡

## ምርጫዎ የእግዚአብሔር መንገድ ነዉ ወይስ የሰይጣን መንገድ?

**ኢያሱ** 24፡ 15 «የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን፡፡»

እግዚአብሔር <u>የሚሰጠን</u>

| |
|---|
| **በተፈጥሮ ወስጥ** |
| ፍፁም ፍጥረት ዓለም |
| የተትረፈረፈ በረከት |
| ሚዛናዊነትና ስርዓት |
| **በአካላችን ወስጥ** |
| ህይወት እና ጤንነት |
| ጤናማ መሻቶች |
| **በአስተሳሰባችን፣በስሜታችንእና በድርጊታችን** |
| ንጹህ ፍቅር በጎ ሐሳቦች የመምረጥ ነጻነት |
| ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት መቃዝዝ፣ ጠቃሚነት፣ ደስተኛነት ከፍርሃት ነጻ መሆን፣ |
| ትህትና፣ ዓላማ እውነት፣ እምነት፣ ፍትህ፣ ሰላም፣ ታማኝነት፣ ጥበብ የፈጠራ ችሎታ፣ ደስታ፡፡ |

<u>ሰይጣን የሚሰጠን</u>

| |
|---|
| **በተፈጥሮ ወስጥ** |
| የተበከለ ተፈጥሮ |
| ስርዓት አልባነት ደህነት |
| ቅርፅ ዓልባነት ርሐብ |
| **በአካላችንወስጥ** |
| በሽታና ሞት |
| ክፋት |
| የስጋ ምኞት |
| **በአስተሳሰባችን፣በስሜታችንእና በድርጊታችን** |
| የኃጢአት ባሪያነት |
| ከእግዚአብሔር መለየት ዓመጸኛነት ራስ ወዳድነት፣ ወዳድነት፣ ወንጀል፣ ዓላማቢስነት፣ ጦርነት፣ ጥላቻ፣ |
| ክፉ ሐሳብ፣ ጥፋት፣ ሐዘን፣ ዓለማማ፣ ትዕቢት፣ ተጠራጣሪነት፣ ስህተት፣ አፍትሐዊነት፣ ፍርሃት፣ ጠብ፣ ወደቀት፡፡ |

| ይህን **ይስሩ** |
|---|
| በሰንጠረዡ ወስጥ ከተዘረዘሩት መካከል ከሚፈልጉኣቸው ጎን የ (x)ምልክት ያድርጉ በሚዩፈልጉአቸው ጎን ደግሞ ( ()ን ያድርጉ፡፡ |

ምልክት ባደረገት መቅረት መሆን የሚፈልጉት ከእግዚአብሔር ጎን ነዉ ወይስ ከሰይጣን?------------------
--------------------------------------------------------------------
----------------------------

# ክፍል 4

## ዓለም ምን ተስፋ አላት?

### አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ለዓለም ግድ ይለዋል፡፡

ምንም እን● ሐጢአተኞች ብንሆን አሁንም እግዚአብሔር ይወደናል፡፡ ከኃጢአት፣ ከሰይጣን፣ እና ከዘላለም ሞት እኛን የሚያወጣበት መንገድ አዘጋጅቷል፡፡ አሁንም ቢሆን ፍጥረተ ዓለምን የሚገዛ እግዚአብሔር ስለሆነ አንድ ቀን ምድርን ሁሉ እንደገና ወደመታዘዝ ያመጣታል፡፡

### የእግዚአብሔር ልጅ የእኛን ቅጣት ተቀበለ

በምድር ላይ ማንኛወም ሰው ኃጢአትን የሰራ እና የሞት ፍርድ የተወሰነበት ነው፡፡ ራሳችንን የምናድንበት ምንም መንገድ አልነበረንም፡፡ እግዚአብሔር እጅግ ስለወደደን የእኛን ቅጣት ይቀበል ዘንድ አንድያ ልጁን ጌታ አየሱስ ክርስቶስን ላከው፡፡

የዛሬ 2000 ዓመት አካባቢ አየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በመምጣት መለኮታዊ በሆነ መንገድ ከአንድ ድንግል ሴት በፍልስጤም ምድር ተወለደ፡፡ የእግዚአብሔርን እወነት እና ፍቅሩን ለሰዎች አስተማረ፣ በህይወቱ ሁሉ ምንም ስህተት አልፈጸመም፡፡ እያንዳንዱን ሰው በአክብሮት እና በርህራሔ ያይ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደወንጀለኛ ተቆጥሮ በመስቀል ላይ ተሰቀለና ሞተ፡፡ ለኃጢአታችን ሲል ሞተ፡፡ እግዚአብሔር አየሱስን ከሞት በሶስተኛው ቀን

በሕይወት በማስነሳት ልጁ መሆኑን ለአለም ሁሉ አሳየ፡፡ ከሞት ከተነሳ ከአርባ ቀናት በኋላ ኢየሱስ ተመልሶ ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ ከትንሳኤው በኋላ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያዩት የኢየሱስ ወዳጆች በወንጌላት ላይ ስለዚህ ታሪክ ነግረውናል፡፡

## ኢየሱስን መቀበል የእግዚአብሔር ልጆች ያደርገናል፡፡

ዕርሱ ቅጣታችንን ስለተቀበለ አዳኛቸው አድርገው የሚቀበሉት ከኃጢአት ኃይል ነጻ ይወጣሉ፡፡ ከኃጢአታችን ስንመለስ እግዚአብሔር ህይወት ይሰጠን እና ልጆቹ ያደርገናል፡፡ በልጁ በሞቱ ከኃጢአት እንድንድን እግዚአብሔር ያሳስበናል፣ ሆኖም ግን አያስገድደንም፡፡

**ሮሜ** 5፡ 17 «በአንድ ሰው መተላለፍ ምክንያት ሞት በዚህ ሰው በኩል የነገሰ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ ጸጋና የጽድቅ ስጦታ የተቀበሉት፣ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት አብልጠው በሕይወት አይነግሱ፡፡»

**የሚከተሉትን ጥቅሶች በማጥናት በቃልዎ ይያዙ**

1ዮሐ 3፡ 16 «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከመስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና፡፡»

**ሮሜ** 6፡ 23 «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፣ የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው»፡፡

## ፍጹም በሆነች ዓለም ውስጥ መኖር ይችላሉ

ዓለምን ከኃጢአት ሊያነጻ እና ሁሉን ነገር አዲስ ለማድረግ ኢየሱስ አንድ ቀን ተመልሶ ይመጣል፡፡ አሁን አዳኝዎ አድርገዉ ከተቀበሉት በዚያን ጊዜ ፍጹም በሆነ ደስታ ውስጥ ከእርሱ ጋር ይኖራሉ፡፡ አሁን በሚኖሩት ህይወትም ኢየሱስ በውስጥዎ ለመኖር ስለሚመጣ የተሻለ ህይወት እንዲኖርዎና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር እንዲያደርጉ ያስችልዎታል፡፡

ለእግዚአብሔር ልጆች የተዘጋጀውን በረከት ከዛሬ ጀምረዉ ተካፋይ መሆን ይችላሉ፡፡

### ይሚከተለውን ይስሩ

**በክፍት ቦታዎች ላይ ስምዎን ይጻፉ**

የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከሰጥ ድረስ ______________________ እንዲሁ ወደልና፡፡

ኢየሱስን አዳኝዎ አድርገዉ አሁን መቀበል ከፈለጉ የሚከተለዉን ጸሎት ይጸልዩ፡፡

## ጸሎት

*እግዚአብሔር ሆይ ስለወደደከኝ እና ስለኃጢአቴ ይሞት ዘንድ ልጅህን ስለላከው አመሰግንሃለሁ፡፡ አሁን ኢየሱስን አዳኜ አድገጌ እቀበላለሁ፡፡ በቀረው የሕይወት ዘመኔ ሁሉ ከሰይጣን ጎን ሳይሆን ከአንተ ጎን መሆን እፈልጋለሁ፡፡ እንደሆንልህ የምትፈልገውን አይነት ሰው ታደርገኝ ዘንድ እለምንሃለሁ፡፡በኢየሱስ ስም፡ አሜን፡፡*

<u>ክፍለ ትምህርት አንደን በማጠናቀቅዎ እን•ን ደስ አለዎ!</u>

በዚህ አጭር የመማሪያ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ወደቀረቡ የትምህርቱ መከለሻ ጥያቄዎች በመሄድ የክፍለ ትምህርቱን ጥያቄዎች ይመልሱ፡፡ ከዚያም ወደ ሚቀጥለዉ ትምህርት በመግባት ጥናትዎን ይቀጥሉ፡፡

*እግዚአብሔር ይባርክዎ!*

# <u>2.ስለ እግዚአብሔር ያለው እውነት ምንድን ነው?</u>

## በዚህ ክፍለ ትምህርት የሚከተሉትን ያጠናሉ፡፡

- ስለ እግዚአብሔር እውነቱን ማወቅ ያለብዎ ለምንድን ነው?
- ስለ እግዚአብሔር እውነቱን የሚያወቁት እንዴት ነው?
- እግዚአብሔር ማንን ይመስላል ?

- እግዚአብሔር እንዴት ነው እንዲያመልኩት የሚፈልገው?

# ክፍል 1

## ስለእግዚአብሔር እውነቱን ማወቅ ያለብዎ ለምንድን ነው?

## ስለእግዚአብሔር እውነቱን ማወቅ ያለብዎ

### ከእግዚአብሔር ማንነት የተነሳ ነው፡፡

እግዚአብሔር የፍጥረተ ዓለም ሁሉ ፈጣሪ፣ ገዢ እና ዳኛ ነው፡፡ ፈጣሪ ስለሆነ ያለውን ነገር ሁሉ ፈጥሯል፡፡ ገዢ እንደመሆኑ መጠን ለፍጥረቱ ሁሉ እና ለዓለም የሚበጅ መልካም ህግጋት አሉት፡፡ ዳኛ እንደመሆኑ መጠን በሚከጠቱ ምላሽ መሰረት በሰዎች ሁሉ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ይወስናል፡፡ እግዚአብሔር ፈጣሪዎ፣ ገዢዎ እና አዳኝዎ ስለሆነ ስለእርሱ እና ለእርስዎ ስላለው እቅድ ማወቅ ይኖርብዎታል፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር የሚወድዎ አባት ስለሆነ እውነተኛ ደስታ ይሰጥዎታል፡፡ ፍቅሩን እና በረከቶቹን በደስታ ለመቀበል እርሱን ማወቅ አለብዎ፡፡

### ለእርስዎ የሞት እና የሕይወት ጉዳይ ስለሆነ ነው

ሕይወት ሰጪው እግዚአብሔር ነው፡፡ በአሁኑ ዓለም የተሻለና ሙሉ ሕይወት፤ ከሞት በኋላ ደግሞ መጨረሻ የሌለው ፍጹም ሕይወት ይሰጥዎታል፡፡

| |
|---|
| **ይህን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙ**<br>ዮሐ 17፡ 3 «እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አንተንና ያላከውንም ኢየሱስን ያወቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት፡፡» |

### እግዚአብሔርን ለማስደሰት እርሱን ማወቅ ስላለብዎ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ልጆች እርሱን ይወዱታል፡፡ ደስ ሊያሰኙትም ይፈልጋሉ፡፡ ኢየሱስን አዳኝዎ አድርገው ተቀብለው ከሆነ አሁን የእግዚአብሔር ልጅ ነዎ፡፡ ሰማያዊ አባትዎን በየእለቱ በተሻለ ሁኔታ ማወቅ እና የሚወደውንም በማንዘብ በሚያደርጉት ሁሉ የሚያስደስቱበትን መንገድ ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡ በሕይወትዎ ትልቅ እርካታ የሚያገኙት በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም የተፈጠሩት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ነገሮችን ለመፈጸም ነው፡፡

| |
|---|
| **የሚከተለውን ይስሩ**<br>በክፍት ቦታዎች ላይ ይሙሉ<br>ስለእግዚአብሔር እውነቱን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም |
| • ከእግዚአብሔር_______________ ነው፡፡<br>• ለእኔ የ_______________ እና_______________ ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡<br>• እግዚአብሔርን_______________ እርሱን_______________ ስላለብኝ ነው፡፡ |

- በዮሐ 17፡ 3_______________ ላይ  አንተንና የላከውንም ያወቁ ዘንድ ይህች_______________ ናት፡፡

# ክፍል 2

## ስለ እግዚአብሔር እውነቱን ማወቅ የሚቻለት እንዴት ነው?

### ስራዎቹን በማየት

ስራውን በማየት ስለአንድ ሰው የምሚረው ነገር ይኖራል፡፡ እግዚአብሔር የሰራትን ዓለም ሲመለከቱ እርሱ ጥበበኛ እና ብርቱ መሆኑን ያወቃሉ፡፡

**ሮሜ 1፡ 20** «ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የሚይታየው የእግዚአብሔር ባህሪ ይኸውም  ዘላለማዊ ኃይሉና መለኮትነቱ፣ ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል፣ ስለዚህ ሰዎች   ማመካኛ የላቸውም፡፡»

### ከሌሎች

ስለ አንድ ሰው ምንነት ማወቅ ከፈለጉ በግል ከሚያወቁት ሰዎች ማወቅ ይችላሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ እግዚአብሔርን በግላቸው ያወቁ ስለነበሩ ሰዎች አስደናቂ ዘገባዎች እናነባለን፡፡ አነጋግሯቸዋል፣ ችግራቸውም ተፈቶላቸዋል፣ እንዲሁም ችግሮቻቸውን አሟልቶላቸዋል፡፡ አካላቸውን ፈውሶ ደስታን ጨምሮላቸዋል፡፡ እግዚአብሔር አልተለወጠም፡፡ ዛሬ በእያንዳንዱ አህጉር በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እግዚአብሔርን ያወቁታል ይወዱታል፡፡ ደንቅ መሆኑንም ይነግሩዎታል፡፡

**1ዮሐ 1፡ 3** «እናንተም ከእኛ ጋር ህብረት እንዲኖራችው ያየነውንና የሰማነውን እንነግራችኋለን ኅብረታችንም ከአብ፣ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው»፡፡

### በቃሉ ከሚናገረዙ

አንድን ሰው ከጽሐፎቹ ወይም ከሚናገረው ነገር በማንሳት ማወቅ ይቻላል፡፡ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ያነጋግርዎታል፡፡ በዚያ ወስጥ የእግዚአብሔርን ባህሪ፣ እቅዶቹ፣ ስጦቹ፣ እና ለእርስዎ ያለውን ፍቅር ያገኛሉ፡፡

**ዮሐ 5፡ 39** «መጽሐፍትን ትመረምሩላቸሁ ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው»

### በግል ልምምድ

**እንደገ** ሰው አብረውት በመኖር፣ በመናገር እና አብረው በመስራት በማባ ሊያውቁት ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔርም በዚህ መንገድ እንደናውቀው ስለፈለገ በሰዎች መካከል ይኖር ዘንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከው፡፡ ኢየሱስ እንደ አባቱ ስለሆነ በእርሱ ወስጥ የእግዚአብሔርን ማንነት ማየት ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔርን በክርስቶስ በኩል ማወቅ ይችላሉ፡፡

**ዕብ** 1፡ 1-3 «እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት በኩል ለአባቶቻችን ተናግሮ፣ በዚህ በመጨረሻ ዘመን ግን በልጁ ለእኛ ተናገረን፡፡ እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና የባህሪዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ በኃያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዞአል፡፡»

ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝዎ አደርገው ሲቀበሉ እግዚአብሔርን ይገልጥልዎታል፡፡ በጸሎትር እና ቃሉን በማንበብ ሲያነጋግሩት የእርሱን መገኘት አስበው በሚያውቁት እና በተሻለ ሁኔታ ሊያውቁት ይችላሉ፡፡

**ዮሐ** 14፡ 21፣23 «የሚወደኝ ትእዛዜን ተቀብሎ የሚጠብቅ ነው፣ የሚወደኝም አባቴ ይወደዋል ወደ እርሱ እንመጣለን ከእርሱም ጋር እንኖራለን፡፡»

**<u>የሚከተለውን ይስሩ</u>**

ከእግዚአብሔር ጋር መተዋወቅ የሚችሉባቸው የሚከተሉት አምስት መንገዶች ተዘርዝርዋል፡፡ በሁሉም በኩል እያወቁት ነውን?

መጀመር ወይም የበለጠ ማድረግ በማገቡዎት ነገሮች ላይ ያስምሩባቸው፡፡

- በተፈጥሮ ወስጥ ስራዎቹን በማየት
- እግዚአብሔርን እና ቃሉን የሚያውቁ ሰዎችን በማዳመጥ
- የእርሱ መጽሐፍ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
- ስለ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በመማር
- ከእግዚአብሔር ጋር በግል በጸሎት በመነጋገር

# ክፍል 3

## እግዚአብሔር ማንን ይመስላል?

### እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊ መንፈስ ነው

እግዚአብሔር እንደ እኛ በጊዜ፣ በቦታ እና በተፈጥሮ ህጎች የተወሰነ አይደለም፡፡ ለዘላለም የነበረና የሚኖር ነው፡፡ መንፈሱ በሁሉ ቦታ አለ፡፡ ሁሉን ያወቃል ሁሉን ማድረግ ይችላል፡፡

### እግዚአብሔር ሶስት አካል አንድ አምላክ ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ስብዕና ያለው አካል ሳይሆን የሚቆጣጠር ኃይል ነው ብለው ያስባሉ፡፡ እኛ ግን ስብዕና ማንነት ያለው እንደሆነ እናወቃለን ምክንያቱም ያስባል፣ ይሰማዋል፣ እንዲሁም ይሰራል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሶስት አካል ያለው አንድ አምላክ /አሀዱ ስሉስ/ እንደሆነ ያስተምረናል፡፡ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በባህሪያቸው፣ በኃይልና በዓላማ አንድ ናቸው፡፡ ፍጹም በሆነ ህብረት እንደ አንድ አካል አንድ አምላክ ሆነው ይሰራሉ፡፡

**ማቴ** 28፡19 «በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው፡፡»

## እግዚአብሔር ፍቅር ነው

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡ ይህ ደግሞ ባህሪው ነው፡፡ ሁሉንም ይወድዳል እንዲሁም ለህይወትዎ የተሻለውን ነገር ሊሰጥዎ ይፈልጋል፡፡ ከዚያም ባሻገር በሰማዩ ባዘጋጀው ድንቅ መኖሪያ ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ ይፈልጋል፡፡

1ዮሐ 4፡8 «የሚዉወድ ግን እግዚአብሔርን አያውቅም፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና፡፡»

## እግዚአብሔር ፍጹም ነው

እግዚአብሔር ፍጹም መልካም፣ ንጹህ፣ እውነተኛ እና በሚያደርገው ሁሉ ትክክለኛ ነው፡፡ ቸር እና እሩህሩህ ነው፡፡

**ማቴ** 5፡48 «ስለዚህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ . . »

## እግዚአብሔር በፅድቅ ይፈርዳል

እግዚአብሔር ቅን እና እውነተኛ ፈራጅ ነው፡፡ ይህ ሁልጊዜ የሚሰራው በእውነት ነው ማለት ነው፡፡ ሁሉንም ስለሚወድ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እርሱን እንዲያውቁት መንገድ አዘጋጀላቸው፡፡ ኢየሱስን ለሚቀበሉት የዘላለም ህይወትን ይሰጣቸዋል፡፡ ኢየሱስን አንቀበልም ብለው ሰይጣንን የሚከተሉት ደግሞ እግዚአብሔር ለሰይጣን ያቀደውን ቅጣት ይቀበላሉ፡፡ በኢየሱስ በኩል ከኃጢአት እና ከሚያስከትላቸው መዘዞች ሁሉ ነጻ ሊያወጣን ይፈልጋል፡፡ ካልፈቀድንለት ግን የተሳሳቱ ተግባሮቻችን የሚያስከትሉትን ችግር እንደንጋፈጥ ይፈቅዳል፡፡

**መዝ** 19፡9 «የእግዚአብሔር ፍርድ የታመነ፣ ሁለንተናወም ጻድቅ ነው»፡፡

**ሮሜ** 3፡26 «እርሱ ራሱ ጻድቅ ሆኖ፣ በኢየሱስ የሚያምነውን የሚያጸድቅ መሆኑን ለማሳየት ነው»፡፡

## እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል፡፡

እግዚአብሔር ያለፈውን፣ የአሁኑን እና የወደፊቱን ያውቃል፡፡ የሚሆነውን ሁሉ ያያል፣ ይሰማል፣ ይረዳልም፡፡ አስተሳሰብዎን እና የሚዜሩትን ሁሉ ለምን እንደሚዜሩ ያውቃል፡፡ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ሁኔታ የተሻለውን ነገር እንዲመርጡ ትክክለኛውንም ወሳኔ እንዲያደርጉ ሊረዳዎ ይፈልጋል፡፡

**ዘፍጥረት** 16፡13 «እርሷም የነገራትን እግዚአብሔርን አልሮኢ ብላ ጠራችው፣ ምክንያቱም የሚያየኝን አሁን አየሁት ብላ ነበርና»፡፡

1ዮሐ 3፡20 «እግዚአብሔር ከልባችን ይልቅ ታላቅ ነውና ሁሉን ነገር ያውቃል»፡፡

## እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው፡፡

ፈጣሪ የሆነው አምላክ የተፈጥሮ ህግ ብለን የምንጠራቸውን ነገሮች በፍጥረተ ዓለም ወስጥ አስቀምጧል፡፡ ሁሉም ነገር የሚንቀሳቀሰው በእነዚህ የተፈጥሮ ስርዓቶች መሰረት ነው፡፡ እግዚአብሔር ከነዚህ የተፈጥሮ ህጎች በላይ

እና በእነርሱ የሚወሰን አምላክ ነው፡፡ ታምራት ተብለው የሚጠሩትን መለኮታዊ ስራዎች ያደርጋል፣ እነዚህ ደግሞ ከሰው ኃይል እና ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ናቸው፡፡

አያሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በርካታ ታምራቶችን አደርጓል፡፡ በሽተኞችን ፈወሷል፡፡ ሙታንን አስነስቷል፣ እንዲህም የሰዎችን ሕይወት ለውጧል፡፡ አሁንም ከሁሉ በላይ የሆነው ሐኪም እና ለስጋችንም ሆነ ለነፍሳችን ጤንነት የሚሰጠን እርሱ ነው፡፡

**ማቴ** 19፡26 «በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ነገር ይቻላል፡፡

**ዘጸ** 15፡26 «ፈዋሻችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና»

**የሚከተለውን ይስሩ**

ከሚከተሉት ሐሳቦች ወስጥ አንዱ ትክክለኛ አይደለም፡፡ ትክክለኛ ያልሆነውን ያስምሩበት፡፡

- እግዚአብሔር ስለሚወደዎ ለረዳዎ ይፈልጋል
- እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣ ጻደቅ አምላክ ነው
- እግዚአብሔር በግል የሚታወቅ አይደለም
- እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ያለውን ማንኛውንም ነገር ይመለከታል፡፡

***ያስተውሉ፦*** እግዚአብሔር እየተመለከተዎ እንደሆነ ማወቅዎ ያስፈራዎታል ወይስ ደስ ይልዎታል? ለምን?

# ክፍል 4

## እግዚአብሔር እንዲያመልከት የሚፈልገዉ እንዴት ነዉ?

በአምልኮ ወስጥ እግዚአብሔርን እንደምንወደው እንደምናከብረው እና ልዕልና እንደምንሰጠው እንገልጻለን፡፡ በተለያዩ አብያተክርስቲያናት እያመሰገንነው ከእርሱ ጋር እንነጋገራለን፡፡ በተለያዩ አብያተክርስቲያናት ወስጥ ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ሲያመልኩ ይመለከታሉ፡፡ እንዴት ነው እንዲያመልከት የሚፈልግ? ደስ የሚያሰኘውስ ምንድን ነው?

## እውነተኛ ቅን ይሁኑ

ይሚፀገሩትን ነገር በእውነት ከልብዎ ማለት አለብዎ፡፡ በእግዚአብሔር ማመን ብቻ ሳይሆን ሊታዘዙትም ፈቃደኛ መሆን አለብዎ፡፡

የሐ 4፡ 24 «እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስ እና በእውነት ለሰግዱለት ይገባል፡፡»

ዕብራዊያን 11፡ 6 «ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት፡፡»

## እግዚአብሔርን ብቻ ያምልኩ

እውነተኛው አምላክ ፈጣሪዎ ብቻ ነው፡፡ ወደ ሌሎች አማልዕክቶች፣ መናፍቶች፣ ምስሎች፣ ወይም ሌሎች ነገሮች እንዳጸልዩ አይፈልግም፡፡

ዘጸአት 20፡ 3 «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ፡፡»

ሐዋ 14፡ 15፣ 17፡ 29 «እናንተ ሰዎች.... እናንተም ደግሞ ከዚህ ከንቱ ነበር ርቃችሁ ሰሚዩንና ምድርን፣ ባሕርንም በወስጣቸውም የሚኖሩትን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር እንድትመለሱ ወንጌልን እንሰብክላችኋለን፡፡»

## ስለበረከቱ ጌታን ያመስግኑ

በጸሎት እና በዝማሬ በፀጥታ እን● ሆነዉ ከልብዎ፣ እግዚአብሔርን ስለፍቅሩ ስለመልካምነቱ እና ስለባረከዎ በረከት ሁሉ ያመስግኑት፡፡

መዝ 98፡ 1 ለእግዚአብሔር አዳስ ዝማሬ አቅርቡ እርሱ ድንቅ ነገሮችን አደርጎአልና» መዝ 150፡ 6 «እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን»

## በትህትና በእምነት ሆነዉ ያምልኩ

ቅዱስ በሆነ አምላክ ፊት ለመቅረብ በራስዎ ብቃትን የሚሰጥ መልካምነት ሊኖርዎ እንደሚዩችል ይረዱ፡፡ ሆኖም ግን እያሱስ አዳኝዎ እንዲሆን እምነዉ ተቀብለዉ ከሆነ እግዚአብሔር ኃጢአትዎን ይቅር ብሎ ልጁ አደርጎ ተቀብሎዎታል፡፡ ስለዚህ ልጅ ከአባቱ ጋር እንደሚ ጋገር እርስዎም በልብዎ ያለወን ሁሉ ለእርሱ ይንገሩት፡፡

## ይሚከተለወን ይስሩ

*ራስዎን ይጠዩቁ፡* በዚህ ክፍለትምህርት በተጠቀሱት አራት መንገዶች እግዚአብሔርን እያመለከት ነው? ይህን ለሚድረግ እቅድ አለኝ?

*እግዚአብሔር ራሱን ለእርስዎ እንዲገልጽልዎ ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ፡፡ እርሱን ብቻ ያምልኩ፡*

<u>ትምህርት ሁለትን ስላጠናቀቁ እን●ን ደስ አለዎ፡፡</u>

በዚህ የመሚሪያ መጽሐፉ መጨረሻ ገጾች ላይ ያሉትን የክፍለ ትምህርት መከለሻ ጥያቄዎች በሞየት ለክፍለ ትምህርት 2 ጥያቄዎች መልሳቸወን ይስጡ፡ ከዚያ በኋላ ወደ ክፍለ ትምህርት 3 በመግባት ጥናትዎን ይቀጥሉ፡፡

*እግዚአብሔር ይባርክዎ፡፡*

# 3. ሕይወት ምንድን ነው?

- **በዚህ ክፍል ትምህርት የሚከተሉትን ነገሮች ይማራሉ**

- *ለምን ዓላማ ተወለዱ?*
- *እግዚአብሔርን የሚያመልኩት እንዴት ነው?*
- *እግዚአብሔርን የሚያስመልኩት እንዴት ነው?*
- *ምን ዓይነት ሰው መሆን ይፈልጋሉ?*
- *የእግዚአብሔር ልጅ መሆንዎን እንዴት ያወቃሉ?*

## ክፍል 1

## ለምን ዓላማ ተወለዱ?

### ለምን እንደተወለዱ ማወቅ አለብዎ

*አንድ ሰው የፕላስቲክ ሳህንን እንደ ምግብ መቀቀያ፣ ብርጭቆን ደግሞ እንደመዶሻ ሊጠቀምበት ሲሞክር ቢያዩ ምን ሊያስቡ ይችላሉ? ዓላማውን ሳያውቅ ሕይወቱን በሙሉ ያባከነ ሰው ሲያዩ ምን ሊሰማዎ ይችላል? ሕይወታችንን ለተፈጠረበት ዓላማ ማዋል እስካልጀመርን ድረስ በዕሳት ላይ የተጣደ የፕላስቲክ ሳህን ወይም እንደ ብርጭቆ መዶሻዎች መሆናችን ነው፡፡ ህይወታችን ያለምንም እርካታ እና መሳካት ያልፋል፡፡*

*እግዚአብሔር ለህይወትዎ ዓላማ እና እቅድ አለው፡፡ በምድር ላይ እንዲሰሩት የሚፈልገው ስራ አለ፣ በሰማዩም ድንቅ መኖሪያ ቤትን አዘጋጅቶልዎታል፡፡ በእግዚአብሔር እቅድ ወስጥ ገብተው ለመኖር ተወልደዋል፡፡*

### የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ተወልደዋል

*እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት፣ ልጁ ለመሆን፣ በፍቅሩ ደስ ለሰኙ፣ እና እርሱን ደስ ለማሰኘት እንደተፈጠሩ ተምረዋል፡፡ ስለዚህ ምንም ነገር ቢያደርጉ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ከሌለዎት የህይወትዎን ዋና ዓላማ አጥተዋል፡፡*

*መዝ* 16፡ 11 *«የሕይወትን መንገድ ታሳየኛለህ፣ በአንተ ዘንድ የደስታ ሙላት፣ በቀኝህም የዘላለም ፍስኃ አለ»፡፡*

**እግዚአብሔርን በመምሰል እንዲያድጉ ተወልደዋል፡፡**

የእግዚአብሔር ልጅ ለሆኑት ለእርስዎ በምድር ላይ ያለው ህየወትዎ ለዘላለም ህይወት የሚዘጋጁበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ ልምምዶችዎ በእግዚአብሔር መንግስት ወስጥ ለሜርዎ ደርሻ የሚያስተምሩ ነገሮች ናቸው፡፡ አሁን የሚያጋጥሞዎት ችግሮች እና ወጣውረዶች ትዕግስትን፣ እምነትን እና መታዘዝን ሊያስተምሩዎ ነገሮች ናቸው፡፡ በመንፈሳዊ ህይወትዎ በሳል እንዲሆኑ እና የበለጠ የሰማዩን አባትዎን እንዲመስሉ ይረዳዎታል፡፡ እግዚአብሔር አሁንም ሆነ ወደፊት የሚጠቀምበዎ ታማኝ ሰው ያደርግዎ ዘንድ ይፍቀዳለት፡፡

2ጢሞ 2፡12 «ብንፀና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሳለን»

**ከእግዚአብሔር ጋር ለመስራት ተወልደዋል፡፡**

በነበሩበት ጊዜ፣ በነበሩበት ቦታ እና በነበረዎ ማንነት የተወለዱት ለቤተሰብዎ ለአካባቢዎ፣ ለአገርዎ፣ እና ለዓለም ሁሉ በረከት እንዲሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር የእርሱ አጋር በመሆን አብረው እንዲሰሩ ይፈልጋል፡፡ ሌሎችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመሩ እና በእርሱ በኩል ወደሚገኝ የተሻለ ህይወት ወስጥ እንዲመሯቸው ያግዛል፡፡

**ኤፌ** 2፡10 «ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ስራ እንድንሰራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ስራዎች ነን፡፡»

**የሚከተሉትን ይስሩ**

- እግዚአብሔር ህይወት የሰጠኝ የእርሱ . . . እንድሆን፣ በእርሱ . . . እንዳድግ፣ እና ከእርሱ ጋር ተባባሪ በመሆን አብሬው ________ ለመሆን ነው፡፡
- *ራስዎን ይጠይቁ*
- በእርግጥ ህይወቴ እግዚአብሔርን ያስደስታል?
- መከራና ወጣ ወረዶች በህይወቴ ትዕግስትን እና መልካም ስነ ምግባርን የሚያመጡ አጋጣሚዎች ናቸው ብዬ እቀበላለሁ?
- ሌሎችን ለመርዳት ማድረግ የምችለውን እያደረኩ ነው?
- የምኖረው ኑሮ ሞት የሁሉ ነገር መጨረሻ እንደሆነ በማሰብ ነው ወይስ ለዘላለም ህይወት ዝግጅት ህይወቴን እየተጠቀምኩበት ነው?
- ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት በማድረግ ደስ ይለኛል?
- በቤቴ እና በአካባቢዬ የእግዚአብሔርን እቅድ መከተል ጀምሬአለሁ?

# ክፍል 2

## እግዚአብሔርን የሚመስሉት እንዴት ነው?

**እግዚአብሔር በአምሳሉ የተፈጠረ መንፈስ ሰጥቶዎታል፡፡**

እግዚአብሔር አዳምን ከምድር አፈር ሰርቶ እንደሌሎች ምድራዊ ፍጡራን አይነት ተፈጥሮ ሰጠው፡፡ ይህን ምድራዊ ተፈጥሮ እርስዎም ወርሰዋል፡፡ የአዳም ወስጣዊ ህይወት፣ መንፈሱ የመጣው ከእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው፡፡ የአዳም መንፈስ እግዚአብሔርን የሚመስል ነበር፡፡ የእርስዎም መንፈስ በብዙ መልኩ እግዚአብሔርን ይመስላል፡፡

**ይህን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙ፡፡**

**ዘፍጥረት 1፡ 26፤ 2፡ 7** እግዚአብሔር «ሰውን በመልካችን ፣ በአምሳላችን እንስራ» በማለት «እግዚአብሔር አምላክ ከምድር አፈር ወስዶ ሰውን አበጀው በአፍንጫው የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ »

በውስጥዎ ያለው የእግዚአብሔር ምሳሌ በብዙ መንገዶች ታይቷል፡፡ ይህ ልዩ መንፈስ ከእንስሳት የተለዩ ያደርግዋል፡፡ ይህን በሰው ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር መልክ የእግዚአብሔር አምሳል ብለን እንጠራዋለን፡፡

- በእርስዎ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን አምሳል በሚከተሉት ነገሮች ውስጥ ማየት ይችላሉ
- ግበረገባዊ ተፈጥሮዎ መልካሙን እና ክፉን ለመለየት ይረዳዎታል፣
- የአድናቂነት ተፈጥሮዎና ወበትን መውደድዎ፣
- የማብብ ችሎታ ያለው ተፈጥሮዎ እውነትን ለማወቅ ያለዎ ፍላጎት፣ የማገናዘብ ችሎታዎ፣ የንግግር ችሎታዎ እና መግባባት መቻልዎ፣
- መንፈሳዊ ተፈጥሮዎ እግዚአብሔርን ለማምለክ ያለዎ ፍላጎት እና ከእርሱ ጋር ህብረት የማድረግ ችሎታዎ፣

የፈጠራ ችሎታዎ አካባቢዎን ለማሻሻል ያለዎ ፍላጎት ሰው ወንዞችን ጠልፎ የመጠቀም፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት እና የሚጠቀምባቸውን መሳሪያዎች የመሥራት ችሎታ አለው፡፡ በሙዚቃ ወስጥ ወበትን መፍጠር፣ ስነ ጥበባዊ ስራዎች፣ ግጥሞች፣ ዝማሬዎች፣ ወዘዋዜዎችን ሁሉ መፍጠር ይችላል፡፡

እነዚህ ነገሮች የሚያመጡት ከእግዚአብሔር ተፈጥሮ ሲሆን ከእንስሳት ልዩ ያደርጉናል፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆኑና በህይወትዎም ልዩ ዓላማ እንዳለው ያሳዩዎታል፡፡

**የሚከተሉትን ይስሩ**

እግዚአብሔር በሰዎች ወስጥ ያስቀመጠው መንፈስ የእርሱ . . . ነጸብራቅና ከ . . . . . . የተለየን ያደርገናል፡፡

በሰው ወስጥ የእግዚአብሔር አምሳል ወበትን በመውደዱና በ . . . . . . ተፈጥሮው፣ በማገናዘብ ችሎታው ወይም በ . . . . . ተፈጥሮው፣ በመሥራት ወይም በመፍጠሩ መልካምን እና ክፉን በማወቁ ተፈጥሮው፣ እግዚአብሔርን በመሻለት ወይም . . . . ተፈጥሮው እንመለከታለን፡፡

እነዚህ ችሎታዎች ከሌሎች የእግዚአብሔር ፍጥረቶች የተለዩ እንደሚያደርጉዎ መረዳት ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔር በሰጠዎ ችሎታ ያደረጉትን አንድ ነገር እንደምሳሌ ያስቡ፡፡ ሌላ ፍጥረት የሌለውን ብዙ ሐሳብና ኃይል ይዘዋል፡፡ ዝንጀሮ መጽሐፍ መጻፍ አይችልም፣ አንበሳ አወሮፕላን ማብረር አይችልም፡፡ እግዚአብሔርን እንዲመስሉ ስለሚያደርግ ስለ እያንዳንዱ ተፈጥሮዎ እግዚአብሔርን ያመስግኑ፡፡

# ክፍል 3

## እግዚአብሔርን የሚመስሉት እንዴት ነው?

**ቁስ አካላዊ አካል አለዎ**

እግዚአብሔር ወሰን የሌለው፣ ዘላለማዊና ሁሉን ቻይ የሆነ መንፈስ ነው፡፡ በቦታም ሆነ በጊዜ አይወሰንም፡፡ አይሞትም፡፡ የእርስዎ መንፈስ ግን የሚኖረው ወሰን አቅም ባለው፣ በአንድ ቦታ ላይ ብቻ መገኘት በሚችል እና አንድ ቀን በሚሞት አካል ወስጥ ነው፡፡ ይህን እንጂ ከእግዚአብሔር የተሰጠዎ ድንቅ ስጦታ ነው፡፡ አካል ስላለዎ መንፈስ ብቻ ቢሆኑ ኖሮ ለሰሩት የማይችሉትን ነገር ለእግዚአብሔር መስራት ይችላሉ፡" አካልዎ የመንፈስዎ መኖሪያ እና እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መቅደስ ስለሆነ ጥንቃቄ ሚዛግ አለብዎ፡፡

1ቆሮ 6፡19፡20 «ለመሆኑ ሰውነታችሁ በወስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታወቁምን ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፡፡»

አንዳንድ ሰዎች ለሚያደርጓቸው መጥፎ ነገሮች በሰውነታቸው ያሳብባሉ፡፡ በራሳቸው መልካም ለማድረግ ብለው ሰውነታቸውን ይቀጣሉ፡፡ አካልዎ በራሱ ጥሩ ወይም መጥፎም አይደለም፡፡ እርስዎ የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነው፡፡ ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ ይወስናሉ ሰውነትዎ ደግሞ ይፈጽመዋል፡፡ ሰውነትን ለመልካም ወይመ ለክፉ፣ ለሰይጣን ወይም ለእግዚአብሔር ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

ሮሜ 12፡1 «እንግዲህ ወንደሞች ሆይ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መስዋእት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሔ እለምናችኋለሁ፡፡»

ሰውነትዎን መቆጣጠርዎን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ ጥሩ አገልጋይ ነወ፤ ነገር ግን በጣም ደካማ ጌታ ነው፡፡ አካላዊ ፍላጎቱ ህይወትዎን እንዲገዛ ከፈቀዳለት ችግር ወስጥ ይገባሉ፡፡ እንዲያወም ለአንዳንድ መጥፎ ልማዶች ተገዢ በመሆን ራስዎን ሊጎዳና ርኩሰት የሆኑ ነገሮችን በመፈጸም እግዚአብሔርን ሊያሳዝኑ ይችላሉ፡፡ የመንፈሳዊ ተፈጥሮዎን ፍላጎት ቸል በማለት የሰውነትዎን ፍላጎት ለማርካት ብቻ ከኖሩ እግዚአብሔርን የመምሰልዎ ነገር እየደበዘዘ ይሄዳል፡፡

## ሐጢአት ተፈጥሮዎን አበላሽቶታል

ሐጢአት በወስጥዎ ያለውን የእግዚአብሔር ምሳሌ አበላሽቶታል፡፡ ሰዎች የራሳቸውን ህይወት ለመምራት ሲሞክሩ እና እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ዓላማ ሲተው እየባሰባቸው ይሄዳል፡፡

ገላቲያ 5፡19 21 «የሥጋ ስራ ግልጽ ነው፡፡ ይህወም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣ ዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠበ፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳደነት፣ መለያየት፣ አድመኝነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ እንዳህም፣ እነዚህን የመሰለው ነው፡፡ አስቀድሜ እንዳልሁ አሁንም አስጠነቅቃችኋለሁ በእንደዚህ ሁኔታ የሚኖሩ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም፡፡»

## በራስዎ ጥረት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይችሉም

እግዚአብሔር ለእርስዎ መልካም ዓላማ ዓለው፡፡ ነገር ግን እርሱ ካላገዘዎ በስተቀር ሊከተሉት አይችሉም፡፡ ምንም ያህል በርትተው ቢሞክሩ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነገር ሁልጊዜ ለማድረግ የሚያስችል ጉልበት አይኖርዎትም፡፡ እርሱ ለለውጥዎ ያስፈልጋል፡፡

ሮሜ 7፡18-20 «በእኔ ማለትም ኃጢአተኛ በሆነው ተፈጥሮዬ ወስጥ ምንም በጎ ነገር እንደሚዩኖር አወቃለሁ በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ ነገር ግን ልፈጽመው

አልችልም፡፡ የሚደርገው ላደርገው የምፈልገውን በጎ ነገር አይደለም ዳሩ ግን ለማድረግ የማልፈልገውን ክፉ ነገር ነው፡፡»

**እግዚአብሔርን ከመምሰል በእጅጉ የራቁ ስለሆኑ በወስጥዎ ሊታደሱ እና ሊለወጡ ይገባል፡፡**

ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ወይም ጥሩ ሰው በመሆን በሚያደርጉት ጥረት ብቻ ራስዎን መለወጥ አይችሉም፡፡ የእግዚአብሔር እርዳታ ያስፈልግዎታል፡፡ ከፈቀዱለት የእርሱን ባህሪ በወስጥዎ እንደገና ይሰራ ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ይልካል፡፡ ያን ጊዜ ብቻ ነው እርሱን ደስ ማሰኘት የሚችሉት፡፡

| **የሚከተሉትን ይስሩ** |
|---|

- እንደ እግዚአብሔር የሚመስሉባቸውን ነገሮች ሲመዘኑ ይህን ክፍል እንደገና ያንብቡ፡፡ በህይወትዎ ወስጥ እንዲኖር በሚፈልጉት ነገር ላይ ያስምሩበት፡፡
- ሰወነታችን ከእዚአብሔር የሆነ ደንቅ . . . . . ______________ ነው፡፡
- . . . . . . . ______ ህይወታችንን እንዲገዛ ከፈቀድንለት እግዚአብሔርን መምሰላችን እየቀነሰ ይሄዳል፡፡

በራስዎ ጥረት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ይችላሉን?

# ክፍል 4

| **ምን ዓይነት ሰው መሆን ይፈልጋሉ?** |
|---|

አንድ ሸክላ ጥራት ያለው ወይም የሌለዉ ዕቃ ሊሆን ይችላል፡፡ ወጤቱ የሚወሰነው በባለቤቱ ፍላጎት እና በሸክላ ሰሪው መሆ ነው፡፡ የሰው ተፈጥሮ ብቻውን ከተተወ ከመጀመሪያት አልፎ ወደከፋ ነገር እየባሰበት ይሄዳል፡፡ በቆሻሻ ነገር የተሞላ የጥላቻ ሐሳብ እና ክፉ ተግባር የሞላበት ይሆናል፡፡ ይሆን እንጂ ጥበበኛ በሆነው ሸክላ ሰሪ በእግዚአብሔር እጅ ከሆነ ግን ህየወትዎ የአስደናቂ ወበት ጠቃሚት ምሳሌ ይሆናል፡፡

**ሮሜ** 12፡ 2 «መልካም ደስ የሚያሰኝ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታወቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን አለም አትምሰሉ፡፡

| **የሚከተሉትን ይስሩ፡፡** |
|---|
| እግዚአብሔር ወስጥዎን እንዲያደስልዎ እና እንዲለውጥዎ ይፈልጋሉ? |

በራስዎ አባባል እንዲያደርግልዎ ይጠይቁት፡፡

ክርስቲያን ከሆኑ ደግሞ እግዚአብሔርን መምሰል ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ ለእርሱ ይንገሩ እና እንዲረዳዎ ይፀልዩ፡፡

# ክፍል 5

## የእግዚአብሔር ልጅ መሆንዎን እንዴት ያወቃሉ?

- ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝዎ አድርገዉ በሚቀበሉበት ደቂቃ ወስጥ እግዚአብሔር ልጁ አድርጎ ይቀበልዎታል፡፡ ይህን ደግሞ በሚከተሉት ሶስት መንገዶች ያሳወቃል፡፡
- ስለዚህ በሚናገረው በቃሉ አማካኝነት
- መንፈስ ቅዱስ በወስጥዎ በሚጥዎ ሚረጋገጫ እና ምስክርነት
- በህይወትዎ በሚሆነው ለወጥ፡፡

ሮሜ 12፡ 1 «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰዉነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያዉ መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሔ እለምናችኋለሁ»

1ዮሐ 5፡ 10-12 «በእግዚአብሔር የሚያምን ሁሉ በልቡ ምስክር አለዉ. . .ምስክርነቱም ይህ ነወ፤ እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት ሰጠን፤ ይህም ሕይወት ያለዉ በልጁ ነው፡፡»

ሮሜ 8፡ 16 «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል፡፡ »

<u>ክፍለ ትምህርት 3 ን ስላጠናቀቁ እን•ን ደስ አለዎ!</u>

የክፍል ትምህርት 3ን ጥያቄዎች በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ገጽ ላይ ከሚገኘው የክፍለ ትምህርት መከለሻ ጥያቄዎች ወስጥ መልሳቸወን ይስጡ፡ ከዚያም ወደ ክፍለ ትምህርት 4 በመግባት ጥናትዎን ይቀጥሉ፡፡

*እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ!*

# 4.የሚያስፈልግዎን ዋና ነገር ማሟላት የሚቻሉት እንዴት ነው?

**በዚህ ክፍለ ትምህርት ወስጥ የሚከተሉትን ይማራሉ፡፡**

- የሚያስፈልግዎ ዐብዩ ነገር ምንድን ነው?
- ይህን የሚያስፈልግዎ ዐብዩ ነገር አያሱስ እንዴት የሚያሟላዉ እንዴት ነው?
- አያሱስ አዳኝዎ ነዉን?
- ሌሎች ፍላጎቶችዎስ?

## ክፍል 1

| የሚያስፈልግዎ ዋና ነገር ምንድን ነው? |
|---|

### ለአካልዎ ወይስ ለነፍስዎ?

በምድረ በዳ ወይም በጫካ ወስጥ የጠፋ ሰው ወይም በታን● የሚሄድ ሰው አቅጣጫዎን በስት ተፈልጎ መዳን አለበት፡፡ የተራበ ሰው ምግብ ያስፈልገዋል፣ የተፈረደበት ዕስረኛ ምህረት ያስፈልገዋል፡፡ በመርዝ የተጎዳ ሰው መፍትሔ ያስፈልገዋል፡፡

እነዚህ ሁሉ ነገሮች በጣም አስፈላጊዎች በሆኑም ሌላ የሚያስፈልግዎ የበለጠ ነገር አለ፡፡ ከአካል ያለፈ ነገር አለዎ፡፡ እርሱም መንፈሳዊ ተፈጥሮ ያለዉ ነፍስዎ ነዉ፡፡ ነፍስዎ በወስጥዎ ያለው የህልዉና ምንጭ ይሁን እንጂ ያለ እዚአብሔር ከሆነ ግን የተበላሸ ነው፡፡ ልክ በወሃ ጥም እንደሚሞት ሰው ይሆናሉ፡፡ ለአካልዎ ከሚያስስፈልጉ አጣዳፊ ነገሮች ይልቅ ለነፍስዎ የሚያስረፈልጉ ሕይወት እና ጤንነት የሚበልጡ ነገሮች ናቸዉ፡፡

**ሮሜ** 5፡12 «ስለዚህ ኃጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደገባ ሁሉ ሞትም በኃጢአት በኩል ገብቷል፣ በዚሁ ማንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም ሁሉም ኃጢአት ሰርተዋል»

### የሚያስፈልግዎ ትልቁ ነገር አዳኝ ነዉ

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን የሰው ነፍስ የጠፋ፣ እየተራበ ያለ፣ ለሞት በሚያደርስ ህመም የታመመ እና ሞት የተፈረደበት ነው፡፡ ሰው ፈልጎ የሚያገኘው፣ የሚመግበው፣ የሚፈውሰው እና ኃጢአቱን ይቅር የሚልለት አዳኝ ያስፈልገዋል፡፡ ትልቁ የሚያስፈልግዎ ነገር አዳኝ የሆነበት ምክንያት ራስዎን ማዳን ስለማይችሉ ነው፡፡

- ክርስቲያን ወላጆች ስላሉዎ አይድኑም
- የቤተክርስቲያን አባል መሆን አያድንም
- ጥሩ ሰው ለመሆን መጣር አያድንዎም
- ያለአዳኝ መዳን አይችሉም

## የሚከተሉትን ይስሩ

ሰው ሊኖረው የሚችለውን ትልቅ ችግር የሚገልጸው የትኛው ሐረግ ነው ከስሩ ያስምሩበት የአካል በሽታ፣ መንፈሳዊ ሞት፣ የምግብ ዕጥረት

እኔ /የራስዎ ስም/ ብዙ የሚያስፈልጉኝ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከሁሉም የሚበልጠው የሚያስፈልገኝ ነገር ...______________ነው፡ ምክንያቱም ራሴን ከኃጢአትና ከሞት. . .________ አልችልም፡፡
ኢየሱስ ክርስቶስን ከዚህ በፊት እንደግል አዳኝዎ አድርገው የተቀበሉ ቢሆንም ይህ ክፍለ ትምህርት አሁንም የሚጠቅምዎ ነገር ነው፡፡ እንዴት በየዕለቱ እንደሚረዳዎ ይነግርዎታል፡፡

# ክፍል 2

## ኢየሱስ የሚያስፈልግዎን ዋና ነገር የሚያሟልዎ እንዴት ነው?

### እግዚአብሔር የላከልዎ አዳኝ ኢየሱስ ነው

ጠፍቶ የነበረውን እና እየተራበ ያለውን ነፍስዎን ፈልጎ ይመግብ እና ከበሽታ ይፈውስ ዘንድ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፡፡ በእኛ ምትክ በመሞት የኃጢአት ይቅርታን ይሰጥዎ ዘንድ ሰው ሆነ፡፡ ስሙ ኢየሱስ ነው፤ ትርጉሙም አዳኝ ማለት ነው፡፡ እርሱ ብቻ ነው ሊያድንዎ የሚችለው፡፡

### ይህን ጥቅስ በቃልዎ ያጥኑ

ሐዋ 4፡12 «ደኅንነት በሌላ በማንም አይገኝም እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና፡፡»

### ኢየሱስ እውነቱን እና መንገዱን ያሳይዎታል

ሰይጣን አዕምሮአችን በስህተት እና በአለማመን አሳውሮታል፡፡ ከእግዚአብሔር ርቀን መንገዱ ጠፍቶብናል ዲያቢሎስ የእግዚአብሔርን ቃል፣ ኃይል፣ ጥበብ፣ መልካምነትና ፍቅር እንድንጠራጠር ሊያደርገን ይሞክራል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከነጭራሹ እግዚአብሔር መኖሩን ይጠራጠራሉ፡፡
2ቆሮ 4፡4 «የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቦና አሳውሮአል፡፡»

ሰይጣን ብዙ ሰዎችን በሐሰተኛ ሐይማኖቶች ያታልላል፡፡ አንዳንዶች ወደ መናፍስት ወይም ምስሎች ይጸልያሉ፡፡

**ሮሜ 1፥23** «የዘላለም አምላክን ክብር ምውት በሆነው ሰው፣ በወፎች፣ በእንስሳትና በምድር ላይ በሚሳቡ ፍጥረት መልክ መስለው ለወጡ፡፡»

ሰይጣን ለእኛ መልካም ስለሆነው እና ክፉ ስለሆነው ነገር ይዋሸናል፡፡ ደስታን ፍለጋ በስህተት መንገድ በመግባት ከሕይዎት መንገድ ርቀን እንገኛለን፡፡

ከሰይጣን በተቃራኒ መልኩ ደግሞ አያሱስ ለፈልገን፣ እና ወደ ደስታ፣ እና የዘላለም ህይወት ለማስገባት ወደ እግዚአብሔር ይመራናል፡፡ በእርሱ እና በትምህርቱ እውቀትን በማወቅ ከአለማመን እና ከስህተት ነጻ መሆን ይችላሉ፡፡

## እነዚህን ጥቅሶች በቃልዎ ይያዙ

**የሐንስ 14፥6** «አያሱስም እንዲህ አለው መንገድ እኔ ነኝ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡»

**ሉቃ 19፥10** «ምክንያቱም የሰው ልጅ የመጣው የጠፉውን ለፈልግና ሊያድን ነው፡፡»

**የሐ 8፥12** «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝም የህይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላለስም፡፡»

**የሐ 8፥32** «እውነትንም ታቃላችሁ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል፡፡ »

ማንም ሰው በቅንነት ወደ እግዚአብሔር ከመጣ እና እውነትን አወቆ ሊኖርበት ከፈለገ እግዚአብሔር ያሳየዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ክፍት በሆነ አእምሮ ይጸልዩ እግዚአብሔር የሚፈልገውንም ለማድረግ ፈቃደኛ ይሁኑ፡፡

**የሐ 7፥17** «ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ የእኔ ትምህርት ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ ያወቃል፡፡»

**ኤፌ 4፥23-24** «ደግሞም በአእምሮአችሁ መንፈስ እንድትታተደሱ እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አያሱስን እንድትለብሱ ነው፡፡»

### የሚከተሉትን ይስሩ

- አያሱስ ወይም ሰይጣን በሚለት መልስ ይስጡ፡
- መልካም ስለሆነው ነገር የሚያሳውረን ማን ነው?
- እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የሚያሳየን ማን ነው?
- ከስህተት እና ከአለማመን ነጻ የሚያደርገን ማን ነው?
- የእግዚአብሔርን ቃል እንደንጠራጠር የሚያደርገን ማን ነው?
- ሰዎችን ወደ ሐሰተኛ ሐይማኖት የሚመራ ማን ነው?

# ፀሎት

*እግዚአብሔር ሆይ እውነትን ያስተምረኝ ዘንድ ልጅህን ኢየሱስን ስለላከው አመሰግንሃለሁ፡፡ እባክህ እውነቱን አሳየኝ፤ የሚከፈለውንም ዋጋ ሁሉ ከፍዬ እንድኖርበት እርዳኝ፡፡*

## ገዳይ የሆነ የልብዎን ኃጢአት ኢየሱስ ያስወግዳል፡፡

ሐጢአት ማለት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መተላለፍ መሆኑን ተምረዋል፡፡ ስለዚህ ከሁሉ የሚብሰው ሐጢአት የእግዚአብሔርን ዋነኛ እና አስፈላጊ ትዕዛዝ መተላለፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ትልቁ ትዕዛዝ ምን እንደሆነ ኢየሱስ ነግሮናል፡፡

ማቴ 22፡ 37-39 «እርሱም እንዲህ አለው፣ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ወደድ፣ ይህ የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው፡፡ ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፣ ይህም ጎረቤትህን እንደራስህ ወደድ፡፡ የሚለው ነው፡፡»

ሁላችንም ሁለቱን የእግዚአብሔርን ዋና ዋና ትዕዛዛት ጥሰናል፡፡ የሐጢአት ሁሉ ስር የሆነው ራስ ወዳድነት ልባችንን ሞልቶ ፍቅራችንን አደብዝዟል፡፡ ለእግዚአብሔር ፍቅር የሰጠነው ምላሽ ምክንያና ብስነት እና ከእርሱ ጋር አለመስማማት ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ወይም ለሌሎች ከምናስበው በላይ ለራሳችን እናስባለን፡፡ በራስ ወዳድነት ላይ ያተኮረው ልባችን በግለሰቦች እና በህዝቦች መካከል ኃጢአተኛን ዓለም ያፈራል፡፡

2ጢሞ 3፡ 2-4 «ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ለዕርቅ የማይሸነፉ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች ችኩሎች፣ በከንቱ በትዕቢት የተወጠሩ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉና፡፡»

## ኢየሱስ ከኃጢአት ሊያነጻዎ እና በእግዚአብሔር ፍቅር ሊሞላዎ መጣ፡

1ዮሐ 1፡ 9፣7 «ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ለለን፣ ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻደቅ ነው፡፡ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ፣ እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ በእርሳችን ህብረት አለን፣ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡»

ሮሜ 5፡ 5 «እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና፡፡»

**የሚከተሉትን ይስሩ**

ሀለቱን የእግዚአብሔር ታላላቅ ትዕዛዞች ጣሰዋልን?

2ጢሞ 3፡ 2-4ን እንደገና ያንብቡና በወስጡ ከተጠቀሱት ኃጢአቶች መካከል በህይወትዎ ቢያንስ አንድ ጊዜ የተላለፉባቸውን ኃጢአቶች ያስምሩባቸው፡፡

እግዚአብሔር ይቅር እንዲልዎ እና በፍቅሩ እንዲሞላዎ ይጠይቁት፡፡

## አያሱስ የኃጢአትን እና የሰይጣንን ኃይል ይሰብራል፡፡

የማይባንን ነገር ማድረግ እስከማንችል ደረስ ኃጢአት የወሳኔ አቅማችንን አዳክሞታል፡፡

**ዮሐ** 8፡ 34 «ኃጢአትን የሚያደርግ የኃጢአት ባሪያ ነው»

**ሮሜ** 7፡ 14፣15፣18 «እኔ ግን ለኃጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥሁ ስጋዊ ነኝ ለማድረግ የምፈልገውን አላደርግም ነገር ግን የምጠላውን ያን አደርጋለሁና በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ ነገር ግን ልፈጽመው አልችልም፡፡»

አያሱስ ከኃጢአት እስራት ነጻ አውጥቶ ከመጥፎ ሱሶች ሁሉ ይፈታል፡፡ ከቁጥጥር ውጪ ከሆነ ቁጣ፣ ከዝሙት፣ ከሙሉል፣ ከስርቆት፣ እና ከወሸት ነጻ ያወጣል፣ ጎጂ ከሆኑ ሱሶች ማለትም ከአልኮል መጠጥ ሱሰኝነት፣ ከሲጋራ፣ ከአደንዛዥ እጾችና እና ከቁማር ነጻ ያወጣል፡፡ የርኩሳን መናፍስትን እና የሰይጣንን ኃይል ይሰብራል፡፡

## የሚከተለውን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙ

**ዮሐንስ** 8፡ 36 «እንግዲህ ወልድ ነጻ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትወጣላችሁ፡፡»

## አያሱስ በእርስዎ ቦታ በመሆን ምህረትን አስገኝቶልዎታል

እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ ስለሆነ ኃጢአትን አያልፍም፡ ሞት እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣበት እና የኃጢአት ወጤት ነው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እጅግ ስለወደደዎ በእርስዎ ቦታ ይሞት ዘንድ አንድ ልጁን ላከው፡፡ አያሱስ የሞተው ለእርስዎ ሞትክ ሆኖ ነበር፡፡ እንደገና በመነሳቱና ወደሰማይ በማረጉ እርስዎም ያንኑ መሆን ይችላሉ፡፡

**1ጴጥ** 2፡ 24 «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ»

ገላ 2፡ 19፡ 20 «ለእግዚአብሔር እኖር ዘንድ፣ በሕግ በኩል ለሕግ ሞቻለሁና፡፡ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፣ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በወስጤ ይኖራል፡፡ አሁንም በሥጋ በምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው፡፡»

እየሱስን እንደ አዳኝዎ አድርገው ሲቀበሉ የዕርሱ ሞት ሞትዎ እንደሆነ ህይቱም ህይወትዎ እንደሆነ መቀበልዎ ነው፡፡ በዚያ ደቂቃ ወስጥ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናሉ፡፡ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ለይቶዎ ነበር፣ ነገር ግን በእየሱስ በኩል ይቅርታን፣ አዳስ ሕይወትን፣ እና ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን ያገኛሉ፡፡

**የሚከተሉትን ይስሩ**

በሐጢአቱ መሞት የለብኝም ምክንያቱም እየሱስ

..............................................................................................................................................................................
....................

እየሱስ ነጻ እንዲያወጣዎ የሚፈልገት ልማድ ካለብዎ ነፃ እንዲያወጣዎ በጸሎት ይጠይቁት

# ክፍል 3

## እየሱስ አዳኝዎ ነዎን?

**ወሳኔው የግልዎ ነው**

እየሱስ አዳኝዎ ለመሆን ፈቃደኛ ነው፣ ነገር ግን እንዲቀበሉት አያስገድድዎ፡

**እርሱን ለመቀበል ጊዜው አሁን ነው፡፡**

በኋላ የሚዩቻልበት እና የተዘጋ ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚያም አልፎ ይህን አዳስ ሕይወት በየቀኑ እየኖሩ መደሰት እንዲችሉ ዛሬ እርሱ የልብዎን በር ያን'ኳ'ል፡፡ ወደ ወስጥዎ ይጋብዙት፡፡

ራዕ 3፡ 20 «እነሆ በደጅ ቆሜ አን'ኳ'ለሁ ዕብራዊያን 3፡ 15 «ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታደንድኑ፡፡»

2ቆሮ 6፡ 2 «እነሆ ትክክለኛው ሰዓት አሁን ነው፣ የመዳንም ቀን አሁን ነው»

**የሚከተለውን ይስሩ**

እየሱስ በአጠገብዎ ስላለ ጸሎትዎን መቀማት ይችላል

በራስዎ አገላለጽ ለኃጢአትዎ ስለሞተልዎ አመስግነዉ አዳኝዎ እንዲሆን ይጠይቁት፡፡ ይህን ወሳኔ ከዚህ በፊት አደርገዉ ከሆነ የሚያስፈልግዎን ሌሎች ነገሮች ስለሚያሟላልዎ በእምነት ያመስግኑት፡፡

# ክፍል 4

## ሌሎች ፍላጎቶችዎስ?

### የሰማዩ አባትዎ ያስብልዎታል

ማቴ 31፡33 «ስለዚህ ምን እንበላለን ምን እንጠጣለን ምንስ እንለብሳለን ብላችሁ አትጨነቁ፣ አሕዛብ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት ይጨነቃሉና የሰማዩ አባታችሁ እነዚህን ሁሉ ለእናንተ እንደሚያስፈልጋችሁ ያወቃል፡፡ ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግስትና ጽደቁን እሹ፣ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል»

### ስለሚፈልጉት ነገር በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገሩ

ፊሊ. 4፡6 «በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለማንኛውም ነገር አትጨነቁ፡፡»

### አየሱስ ፈዋሽዎ ይሆናል

በሚፀለይበት ጊዜ መልስ በመስጠት አየሱስ የታመሙትን ይፈውሳል፡፡

ሐዋ 10፡38 «አየሱስ በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያቢሎስ ስልጣን ስር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ»፡፡

ዕብ 13፡8 «አየሱስ ክርስቶስ ትናንት ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው፡፡»

**ይህን ይስሩ**

ስለሚያስብልዎ ያመስግኑና ስላለብዎ ማንኛውም ችግር እንዲረዳዎ በጻሎት ይጠይቁት፡፡

<u>ክፍለ ትምህርት አራትን ስላጠናቀቁ እን●ን ደስ አለዎ፡፡</u>

*አሁን የክፍለ ትምህርት አራትን ጥያቄዎች በዚህ ትምህርት መጨረሻ ገጽ ላይ ከሚገኙት የክፍለ ትምህርት መከለሻ ጥያቄዎች መካከል መልሳቸዉን ከሰጡ በኋላ ክፍለ ትምህርት አምስትን ያጥኑ፡፡ ስደስቱት ትምህርቶች ካጠናነቀቁ እና ለቿያቄዎች መልሶችዎን ከላኩልን በኋላ ሰርቲፊኬት እንልክልዎታለን*

*እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ!*

# 5.ከሞት <u>በኋላ ምን አለ?</u>

## በዚህ ክፍለ ትምህርት የሚከተሉትን ይማራሉ

ከሞት በኋላ ምን?

መንግስተ ሰማይ እና ሲኦል ምን ይመስላሉ?

ምርጫዎ ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

እንዴት ወደ መንግስተ ሰማይ ይሔዳሉ?

## ክፍል 1

## ከሞት በኋላ ምን?

### የመጀመሪያው ጊዜያዊ ሁኔታ

በሚሞቱበት ጊዜ የሚሆነው ነገር ምንድን ነው? መንፈስዎ ከቁሳዉ ሰውነትዎ ይለያል፡፡ አካል በምድር ላይ ይቀራል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ዓለም ይሆን ዘንድ ተፈጥሯልና፡፡ ይሁን እንጂ ሁልጊዜ ህልውናዎን ያወቃሉ፡፡ አያሱስ ክርስቶስን ተቀብለው ከሆነ ወዲያውኑ ከእርሱ ጋር ለመሆን ይሄዳሉ ነገር ግን ያዘጋጀልዎን የዘላለም ሕይወት አልቀበልም ብለዉ ከሆነ ከእርሱ ተለይተዉ ሲኦል ወደሚባል ቦታ ይሔዳሉ፡፡ ሲኦል የተባለው ቦታ የተዘጋጀው ለሰይጣን እና ለተከታዮቹ ነው፡፡

ሉቃ 16፥ 22፣23 «ይህም ድኻ ሞተ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት ሐብታማም ሰው ደግሞ ሞቶ ተቀበረ፡፡ በሲኦልም እየተሰቃየ፡፡»

አሁን ያለን አካል ለመንግስተ ሰማይ ብቁ አይደለም፡ በምድር ለመኖር ጊዜያዊ ቤት ነው፡፡ ስንሞት ጥለነው እንሄዳለን፡፡ ከአዲሱ ፍጥረት ጋር የሚስማማ ሌላ አካል ወይም መኖሪያ ቤት እግዚአብሔር ተስፋ ገብቶልናል፡፡

2ቆሮ 5፥ 1 «መኖሪያችን የሆነው ምድራዊ ደን●ን ቢፈርስም፣ በሰው እጅ ያልተሰራ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሆነ ዘላለማዊ ቤት በሰማይ እንዳለን እናውቃለን፡፡»

**ትንሣዔ**

ምናልባትም በቅርቡ ኢየሱስ ለእርሱ ለሆኑት ተመልሶ ይመጣል፡፡ በዚያን ጊዜ እርሱን የተቀበሉት ይለወጣሉ፡፡ እንደ እርሱ ዓይነት ለአ አካል ይሰጣል፡፡ ነፍስዎ ከአዲስ አካል ጋር ትነሳለች፡፡

ዮሐ 11፥ 25 «ኢየሱስም እንዲህ አላት «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ በእኔ የሚያምን ቢሞት እን● በሕይወት ይኖራል፡፡»

1ቆሮ 15፥ 42፣43 «የሙታን ትንሣኤም እንደዚሁ ነው፤ የሚበሰብስ አካል ይዘራል፣ የማይበሰብስ አካል ሆኖ ይነሳል፤ በውርደት ይዘራል፣ በክብር ይነሣል፣ በደካም ይዘራል፣ በኃይል ይነሣል፡፡»

ፊሊ 3፥ 20፣21 «እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፣ ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠበቃለን፡፡ እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኃይል፣ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል፡፡»

## ይህን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙ

1ተሰ 4፥ 16፣17 «ጌታ ራሱ በታላቅ ትእዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምጽና በእግዚአብሔር የመለከት ድምጽ ከሰማይ ይወርዳሉ፡፡ በክርስቶስ የሞቱትም አስቀድመው ይነሳሉ፡፡ ከዚያም በኋላ እኛ የቀረነው፣ በሕይወትም የምንኖረው ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን በዚህም መሰረት ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን፡፡»

## የክርስቶስ የፍርድ ወንበር

እንደ እግዚአብሔር ልጆች በምድር ላይ ስለሰራነው እና ለምን እንደሰራነው ስራችን ይመዘናል፡፡ በታማኝነት ለተበረከተ አገልግሎት ሽልማት ይሰጣል፡፡ እግዚአብሔር በዘላለማዊ መንግስቱ ወስጥ የተወሰኑ ኃላፊነቶች እና ክፍሎችን ይሰጠናል፡፡

2ቆሮ 5፥ 9፣10 «ስለዚህ በሥጋ ብንኖርም ወይም ከስጋ ብንለይም ዓላማችን እርሱን ደስ ማሰኘት ነው ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለን፡፡»

**የሺህ ዓመት ዘመን**

ከዚህ ከመጀመሪያው ፍርድ በኋላ ኢየሱስ ከተከታዮቹ ጋር ወደ ምድር ተመልሶ ይመጣል፡፡ ዲያቢሎስ ለአንድ ሺህ አመታት ያህል ይታሰራል፡፡

ኢየሱስም መንግስቱን እና አገዛዙን በምድር ሁሉ ላይ በመዘርጋት ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል በድንቅ ሰላምና ብልጽግና ይገዛል፡፡ ይህ ጊዜ የሺህ ዓመት ዘመን ይባላል፡፡ የዱር አራዊቶች እን● እርስ በእርሳቸው እና ከሰው ጋር በሰላም ይኖራሉ፡፡

ራዕይ 20፥ 4 «እነርሱም ከሞት ተነስተው ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ነገሡ፡፡

ኢሳ 11፥ 6 «ተኩላ ከበግ ጠቦት ጋር ይኖራል፣ ነብርም ከፍየል ግልገል ጋር ይተኛል፣ ጥጃ የአንበሳ ደቦልና የሰባ ከብት በአንድነት ይሰማራሉ፣ ትንሽ ልጅም ይመራቸዋል፡፡» ኢሳ 35፥ 1፣ 5-6 ፣9-10

«ምድረ በዳወና ደረቁ ምድር ደስ ይላቸዋል፣ በረሃው ሐሴት ያደርጋል ይፈካል፣ እንደ አደይም ያብባል፡፡ በዚያን ጊዜም የእወር ዓይኖች ይገለጣሉ፣ የደንቆሮም ጆሮዎች ይከፈታሉ አንካሳ እንደሚዳቋ ይዘላል፣ የዲዳወም አንደበት

በደስታ ይዘምራል፣ የዳኑት ብቻ በዚያ ይሄዳሉ እግዚአብሔር የዋጃቸው ይመለሳሉ እየዘመሩ ወደ ጽዮን ይገባሉ ዘላለማዊ ደስታን እንደ አክሊል ይቀዳጃታል፡፡»

## ያልዳኑት ትንሳዔና ፍርድ

ከሺህ ዓመቱ ንግስና በኋላ በክርስቶስ እና በሰይጣን መካከል የመጨረሻ ጦርነት ይካሄዳል፣ ዲያቢሎስ ወደ እሳት ባህር ይጣላል፡፡ ከዚያም የእግዚአብሔርን የድነት እቅድ ያልተቀበሉት ሙታን እንደገና ወደህይወት ይመጡና ይፈረደባቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን ከመከተል ይልቅ ሰይጣንን መከተልን የሚጡት በሙሉ ለዲያቢሎስ ወደተዘጋጀው የቅጣት ስፍራ ይሄዳሉ፡፡

ራዕ 20፡ 11፣12፣15 «ከዚህ በኋላ ታላቅ ነጭ ዙፋንና በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፡፡ ሙታንን፣ ታላላቆችንና ታናናሾችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ መጻህፍትም ተከፈቱ ሙታንም በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው መሰረት እንደስራቸው መጠን ተፈረደባቸው ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባህር ተጣለ፡፡»

## ዘላለማዊው እጣ ፈንታ

ፃድቃን /ከእግዚአብሔር ጋር የተስማሙ/ እና ልጆቹ የሆኑት እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ሁሉ ለዘላለም ይደሰቱበታል፡፡ የእርሱን ማዳን አንቀበልም ያሉት ደግሞ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ይለያሉ፡፡

ማቴ 25፡ 46 «እነ ዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ፡፡»

### የሚከተሉትን ይስሩ

ትክክለኛውን ቃል ይምረጡ

ከሞት በኋላ መፃፈስ________________ነው፡፡

(ህልውና ያለው፣ ህልውና የሌለው)

የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ያልተቀበሉት ወደ_______________ይሄዳሉ

መንግስተ ሰማይ ፣ ሲኦል

- እያሱስን የተቀበሉት ከሞት በኋላ የሚኖሩት በ_______________ ነው፡፡

መንግስተ ሰማይ፣ ሲኦል

# ክፍል 2

## መንግስተ ሰማይ እና ሲኦል ምን ይመስላሉ?

ከሁለቱ ቦታዎች አንዱ የዘላለም መኖሪያዎ ይሆናል፣

መንግስተ ሰማይ ወይስ ሲያል?

ሰኦል

*ከእግዚአበሔር መለየት*

**ማቴ** 25፡ 41 «እናንተ የተረገማችሁ ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ፡ ፡ »

## መንግስተ ሰማይ

*ከእግዚአብሔር ጋር መኖር*

«**ዮሐ** 14፡ 2 በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ ይህ ባየሆነማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፣ የምሄደው ስፈራ ላዘጋጅላችሁ ነው፡ ፡ »

**ራዕይ** 21፡ 3 «እነሆ የእግዚአብሔር ማደሪያ በሰዎች ማከል ነው እርሱ ከእናንተ ጋር ይኖራል እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፡ ፡ »

መልካም የሆነ ነገር ሁሉ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡ ፡ በእርሱ ዘንድ ያሉት ብርሃን፣ ሕይወት፣ ወበትና ደስታ ናቸው፡ ፡ ከእርሱ ከተለዩ ግን ጨለማ አለ፣ መከራ ሐዘንና ሞት አሉ፡ ፡

ሰኦል

*መከራ*

**ሉቃ** 16፡ 23፣24 «በሰኦልም እየተሰቃየ … በዚህ ነበልባል እየተሰቃየሁ ስለሆነ እያለ ጮኸ፡ ፡ »

**ማቴ** 25፡ 30 «ልቅሶና ጥርስ መፋጨት ወዳለበት በወጭ ወዳለው ጨለማ አወጥታችሁ ጣሉት»

## መንግስተ ሰማይ

*ዘላለማዊ የሆነ ፍፁም ደስታ*

**ራዕ** 21፡ 10፣11 በመንፈስም ወደ አንድ ትልቅና ረጅም ተራራ ወስዶኝ ቅድስቲቱ ከተማ እየሩሳሌም ከሰማይ ከዕግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ እርስዋም በእግዚአብሔር ክብር ታበራ ነበር

**ራዕ** 22፡ 5 «ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም ጌታ አምላክ ስለሚያበራላቸው ፕመብራት ወይም የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም ከዘላለም እስከአላለም ይነግሳሉ፡ ፡ »

| **ሽኦል** | **መንግስተ ሰማይ** |
| --- | --- |
| *መከራ*<br>**ራዕ** 20፥10 እነርሱም ቀንና ሌሊት ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሰቃያሉ፡፡ | *ፍጹም የሆነ ዘላለማዊ ደስታ*<br>**ራዕ** 21፥3፣4 እግዚአብሔር ራሱም . . . እንባን ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል ከእንግዲህ ወዲህ ሞት ወይም ሐዘን ወይም ልቅሶ ወይም ስቃይ አይኖርም፡፡ |

የዘላለም መኖሪያችን በምንመርጥበት ጊዜ ስለሚኖሩን የጎረቤቶች እናስብ፣

| **ሽኦል** | **መንግስተ ሰማይ** |
| --- | --- |
| **ማቴ** 25፥41 ለዲያብሎስ ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ፡፡ | **ዮሐ** 14፣1፣3 እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ፡፡<br>**ዕብ** 12፥22፣23 እናንተ ግን ወደ ጽዮን ተራራ ወደ ሰማያዊት እየሩሳሌም ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ መጥታችኋል፣ በደስታ ወደተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፣ ስማቸው በሰማይ ወደ ተጻፈው ወደ በኩራት ማህበር ቀርባችኋል፣ የሁሉ ዳኛ ወደ ሆነ ወደ እግዚአብሔር ፍጹምነትን ወዳገኙት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፡፡ |

**የሚከተለውን ይስሩ**

«በክፍል 2 ላይ ከተጠቀሱት ጥቅሶች መካከል በዘላለም መኖሪያዎ እንዲሆኑብዎ የሚፈልጉአቸውን ነገሮች ከያዙት ጎን አይሆንብኝ ብለዉ ይፃፉ፡፡ ከሚፈልጉአቸው ጥቅሶች ጎን ደግሞ አዎ ይሁን ብለዉ ይፃፉ፡፡»

# ክፍል 3

## ምርጫዎ ምን ያህል ወሳኝነት አለው?

ሸኦል ስለሚሄድ እግዚአብሔርን መውቀስ የለብዎም፡ ሁሉንም ሊያድን ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው በመንግስተ ሰማይና በሰኦል መካከል መምረጥ አለበት፡፡

ዘዳ 30፡19፣20 «ሕይወትንና ሞትን፣ በረከትንና ርግማንን በፊትህ እንዳስቀመጥሁ እንግዲህ አንተና ልጆችህ በሕይወት እንድትኖሩ ሕይወትን ምረጥ፡ ይህም አምላክህን እግዚአብሔርን እንድትወድ ቃሉን እንድታደምጥና ከእርሱ ጋር እንትጣበቅ ነው፡፡»

መንግስተ ሰማይን ወይም ሰኦልን መርጠዉ በሚሄዱበት መንገድ ሌሎች ተከታዮች ይኖሩዎታል፡፡ ቤተሰቦችዎንና ጓደኞችዎን ወደየትኛዉ ፍፃሜ ለመምራት ይፈልጋሉ?

**የሚከተለውን ያድርጉ**

አያሰስን ወደ እርስዎ ስለላከልዎ እግዚአብሔርን ያመስግኑ፡፡ ከቤተሰቦችዎ መካከል ወደ ሰኦል እየሄዱ ያሉ ካሉ ይጸልዩላቸው፡፡ እንዲያታስጠነቅቃቸው እና ወደ አዳኙ እንዲመሩአቸው ይረዳዎ ዘንድ እግዚአብሔርን በጸሎት ይጠይቁት፡፡

# ክፍል 4

## እንዴት ነው ወደ መንግስተ ሰማይ የሚገቡት?

ሌሎችን ወደ መንግስት ሰማይ ለመምራት ከፈለጉ በመጀመሪያ ደረጃ እርስዎ እርምጃ መውሰድዎን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ ከዚያ በኋላ ወዳጆችዎም እንዲገቡ ይርዱአቸው፡፡

**ከተሳሳተው መንገድ ይወጡ**

ሁላችንም በኃጢአት ጎዳና እየሄድን ከእግዚአብሔር በሩቅ ወደ ሰኦል አቅንተን ነበር፡፡ ከኃጢአታችን ተመልሰን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እና በመንገዱ ለመሄድ ወሰንን፡፡ ስለአመጻችን ይቅር እንዲለን እንለምን ዋለን፡፡ ይህ ወደ መንግስተ ሰማይ ለመሄድ የመጀመሪያው እርምጃ የሆነ ንስሐ ነው፡፡

በሌሎች ላይ የፈጸምነውን በደልም በማንዘብ ለማስተካከል መሞከር አለብን፡፡ ጠላቶቻችንን ይቅር ማለት፣ የበደልናቸውን ይቅርታ መጠየቅ፣ እና ያሰረቅነውን መመለስ አለብን፡፡ ሐጢአታችንን በመሉ ከተናዘዝን ይቅር በማለት በምናደርገው ሁሉ ይረዳናል፡፡

## ይህን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙ

1ዮሐ 1፡ 9 «ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከአመጻ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው፡፡»

2ጴጥ 3፡ 9 «አንዳንድ ሰዎች የዘገዩ የንደሚቆጥሉቸው የተስፋ ቃሉን ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ማንም እንዳይጠፉ ሁሉ ለንስኃ እንዲበቁ ስለ እናንተ ይታገሳል፡፡»

## ትክክለኛውን መንገድ ለይተዉ ይወቁ

እግዚአብሔር የመንገዱ ካርታ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ ሰጥቶዎታል፡፡ መንገዱ አየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ይከተሉት፡፡

## ይህን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙ

ዮሐ 14፡ 6፣ 6፡ 37 «ኢየሱስም እንዲህ አለው፣ መንገዱ እኔ ነኝና፣ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፣ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ወደ እኔ የሚመጣውንም ከቶ ወደ ወጭ አላወጣውም»

## ትክክለኛውን መንገድ ይምረጡ

ይህ ማለት የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን አየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝዎ እና የህይወትዎ ጌታ አደርገዉ መቀበል ነው፡፡ እርሱም እንደሚቀበልዎ በማመን በእርሱ ይደገፉ፡፡

## ይህን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙ

ሐዋ16፡ 31 «በጌታ በአየሱስ እመን፣ አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ»

ዮሐ 20፡ 31 «ነገር ግን አየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንድታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት እንዲኖራችሁ ይህ ተጽፏል፡፡»

## ትክክለኛዉን መንገድ እስከመጨረሻ ይከተሉት

ብቀሪዉ ዘመንዎ ሁሉ አየሱስን ይከተሉት፡፡ መፅሐፍ ቅዱስን ባነበቡና በፀለዩ መጠን ጌታ ራሱ ይመራዎታል፡፡

1ጴጥ 2፡ 25 «ቀደሞ እንደ ጠፉ በጎች ትቅበዘበዙ ነበር አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠበቂ ተመልሳችኋል»

### ይሚከተለዉን ይስሩ

*በዚህኛዉ የትምህርት ክፍል ወደ መንግስተ ሰማይ መሄድ እንደ ጉዞ እንደሆነ ተገልፆአል*
በግልዎ ወደ መንግስተ ሰማይ የሚያደርሰዉን መንገድ አግኝተዉታል?

ካላገኙት አሁን ፈቃደኛ ይሆናሉ?

ለቤተሰዎችዎ ወይም ለሌሎች ለሚያውቁዋቸዉ ሰዎች ስለዚህ የህይወት መንገድ ይንገሩአቸዉ

*ይህን ክፍለ ትምህርት ስለአጠናቀቁ እንኳን ደስ አለዎ!*

<u>እግዚአብሔር ይባርክዎ!</u>

# 6.እዉነተኛዋ <u>ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?</u>

### በዚህ ትምህርት ዉስጥ የሚከተለትን ይማሩሉ

ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነወ?
እዉነተኛ ቤተ ክርስቲያን ምን ታደርጋለች?
የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ለምን አስፈለገ?
በቤተ ክርቲያን ያለዉ እንቅስቃሴ ምንደን ነወ?

## ክፍል 1

## ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነወ?

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ብዙ ትርጉሞች አሉት፡፡

**ለክርስቶስ የተለዩ ሰዎች**

ኢየሱስ ሲናገር «ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ» አለ /ማቴ 16፡18/፡፡ እዚህ ላይ የተጠቀመበት ቃል ትርጉሙ ተለይተው የወጡ ማለት ነው፡፡ እንደንከተለው ጠርቶናል፡፡ አሮጌውን የኃጢአት ህይወት በመተው ኢየሱስን መሪያቸው አደርገው እወቅና በመስጠት ተለይተው የወጡ አካል ብልቶች እንሆናለን፡፡ እዉነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ይህች ናት፡፡ አካሎችን ሁሉ የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ከእነ ዚህም አብዘኞቹ በመንግስተ ሰማዩ ይገኛሉ፡፡

**ቆላስያስ** 1፡18 እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፡፡

ሮሜ 12፡5 እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፡፡ እያንዳንዳችንም የሌለው ብልት ነን፡፡

**አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን**

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ይደረግ እንደነበረው ሁሉ በክርስቶስ አንድ ዓይነት እምነት ያላቸው የአንድ አካባቢ ሰዎች በየጊዜው እየተገናኙ አብረው ያመልኩታል፡፡ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አቋቁመው አብረው ለጌታ ይሰራሉ፡፡

**ማቴ** 18፡20 ሁለት ወይም ሶስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰብበት መካከል በዚያ እገኛለሁና፡፡

**ቆላ** 4፡ 15 በሎዶቅያ ላሉት ወንደሞች ቤቷም ላለች ቤተክርስቲያን ሰላም አቅርቡልኝ፡፡

**አገር አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት**

ቤተ እምነት ማለት በርካታ አጥቢያ ቤተክርስቲያኖቸን የያዘ ድርጅት ነው፡፡ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የሚረዳዱ እና በተናጥል ከመስራት ይልቅ አብረው በመሆን ለጌታ የበለጠ መስራት የሚችሉ ናቸው፡፡ ስነ

ጸሐፎቻቸን ያትማሉ፡፡ አገልጋዮችን ያሰለጥናሉ፡፡ አዳዲስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን ይከፍታሉ፡፡ እንዲሁም ትምህርት ቤቶችን እና የወላጅ አልባ ልጆች ማደጊያ ቦታዎችን ያንቀሳቅሳሉ፡፡

የአገር አቀፉ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት መሪዎች ሐዋሪያው ጳወሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ያደርግ እንደነበረው ሁሉ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች በችግራቸው ይረዷቸዋል፡፡

*ሐዋሪያት ሥራ* 15፡6፣ 23፣41 ሐዋሪያትና ሽማግሌዎችም ይህንኑ ጉዳይ ለማጤን ተሰባሰቡ፡፡ በእነርሱም እጅ.. ደብዳቤ ላኩ. . . አብያተ ክርስቲያናትንም እያበረታቱ በሶሪያና በኪልቅያ በኩል አለፉ፡፡

ስለትክክለኛ የአምልኮ ስርዓት፣ ስለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እና ስላንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ትርጉም አሰጣጥ ላይ በሚፈጠሩ ልዩነቶች ምክንያት የተለያዩ ቤተ እምነቶች ተፈጥረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ ቤተ እምነቶች በዋና ዋና ነጥቦች ላይ በመስማማት በአገልግሎትም ሆነ በአምልኮ ይተባበራሉ፡፡

እንዲሁም ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድ ላይ የሚሰበሰብበት ሕንጻ ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ትልቅ ይሁን ትንሽ በጣም በጌጣጌጥ ያሸበረቀ ወይም ምንም የሌለው ሊሆን ይችላል፡፡ ዋናው ቁም ነገር የእግዚአብሔር በቦታው መገኘት እንጂ የአዳራሹ ይዘት አይደለም፡፡

# ክፍል 2

## እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ምን ታደርጋለች?

በዚህና በክፍል ሶስት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የሚያመለክተው በአጥቢያ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የምትንቀሳቀሰዋን የክርስቶስ አካል ነው፡፡

### እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ትወዳለች ለእርሱም ትኖራለች፡፡

እግዚአብሔር ፍጹም በሆነ ፍቅር እንድንወደው ይፈልጋል፡፡ የፈጠረን ልጆቹ እንድንሆን በፍቅሩ ደስ እንዲለንና እንድንወደው ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር የምትገናኝ በአምልኮ ነው፡፡ በግል እና በሕብረት ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር በጸሎት፣ በውዳሴ፣ በዝማሬ፣ በመስጠት፣ በማገልገል እና ለትዕዛዙ ታዛዦች በመሆን ይገልጻሉ፡፡

### እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ስለ ኢየሱስ ለዓለም ትመሰክራለች፡፡

እያንዳንዱ ክርስቲያን ለቤተሰቦቹ እና ለጓደኞቹ እንዴት ሊድኑ እንደሚችሉ መናገር አለበት፡፡ የወንጌል መልዕክት በዓለም ሁሉ ለማዳረስ እንድንችል መንፈስ ቅዱስ ያግዛል፡፡

### ይሚከተሉትን ጥቅሶች በቃልዎ ይያዙ

**ማር** 5፡19 **«ወደ** ቤትህ ሂድ ለዘመዶችህም ጌታ ምን ያህል ታላቅ ነገር እንዳደረገልህና ያሳየህን ምሕረት ንገራቸው**»**

ማር 16፡15 **«ወደ** ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበክ**»**

ሐዋ 1፥ 8 «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይል ትቀበላላችሁ እስከ ምድር ዳርቻ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ»

## እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ታስተምራለች

ቤተ ክርስቲያን በሚቻለው መንገድ ሁሉ ለምዕመናን የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በማስተማር የአያሰብ ተከታዮች ታደርጋለች

ማቴ 28፥ 19-20 «ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርቴ አድርጉአቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው»

## ቤተ ክርስቲያን ለምዕመኖች ትጠነቀቃለች

ቤተ ክርስቲያን መደበኛ የአምልኮ ጊዜ በማዘጋጀት የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት በማካሄድ ሕብረት በመፍጠርና በማገልገል መንፈሳዊ እድገት እንዲኖር ታደርጋለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን ችግር ላለባቸው እርዳታ ታደርጋለች የምክር አገልግሎትም ትሰጣለች፡፡

# ክፍል 3

## ቤተ ክርስቲያን ስለሚያስፈልግዎ

በመንፈሳዊ ነገር የሚረዱና የሚያስተምሩ ሰዎችን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ወስጥ አስቀምጧል፡፡ በዚህ መንገድ መንፈሳዊ ፍላጎቶችዎን ያሟላል፡፡

ኤፌ 4፥ 11፥ 12 «አንዳንዶች ሐዋሪያት አንዳንዶች ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች ሌሎቹ ደግሞ እረኞች አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፡፡ ይህውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ስራ ለማዘጋጀት፡፡»

ወደ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል ያለብዎ በገንዘብ፣ በምግብ፣ ወይም በሌሎች ቁሳቁሳዊ ነገሮች ርዳታ አገኛለሁ በሚል ዓላማ መሆን የለበትም፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን በሕይወትዎ ሲያስቀድሙ የሚያስፈልጉዎን ነገሮች ደግሞ እርሱ ያሟላል፡፡

## ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ስለሆኑ

እያንዳንዱ የአካሉ ክፍል የሚሰራው ስራ አለ፡፡ የክርስቶስ አካል ብልት እንደመሆንዎ ማከናወን የሚገባዎት ስራ አለ፡፡ ጣቱ በራሱ ብቻውን ጠቃሚ መሆን ካለበት ከእጅ ጋር መገናኘት አለበት፡፡ እንዲሁ ሁሉ እርስዎም በህይወትዎ ለእግዚአብሔር የመጀመሪያውን ስፍራ በመስጠት ሌሎችን ለመርዳት እግዚአብሔር እንዲጠቀምብዎ ይፍቀዱለት፡፡

ሮሜ 12፥ 4፣6 «እያንዳንዳችን በአንዱ አካላችን ብዙ ብልቶች እንዳሉን እንዚህም ብልቶች አንድ አይነት ተግባር እንደሌላቸው ሁሉ እንደተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን፡፡»

## እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ የሚያገለግሉት በቤተክርስቲያን ወስጥ ስለሆነ ነው፡፡

የወኃ ጥምቀት ስርዓትን በሚፀም ቤተ ክርስቲያንን መቀላቀልዎ ለሌሎች ጥሩ ምክር መሆንና ለእግዚአብሔርም መስጠትና መታዘዝ ነው፡፡ ካለዎ በመስጠትም እግዚአብሔርን ያገለግላሉ፡፡ ይህን በሁሉም ቦታዎች የሚሰራ ወንጌል ለማዳረስ ገንዘባቸዉ በመስጠት የሚያገለግሉ ብዙ ናቸው፡፡ እርስዎ ለወንጌል ስራ ገንዘብ የሰጠ ሰው ስለነበረ ወንጌልን ለሰሙ ችለዋል፡፡ እርስዎም በመስጠትዎ ምክንያት ሌሎች ወንጌልን ይሰሙ፣ ይደናሉ፡፡

2 ቆሮ 9፡6፡7 «ይህን አስታውሱ ጥቂት የዘራ ቂት ያጨዴል ብዙ የሰራ ብዙ ያጨዴል፡፡ እያንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግደታ ሳይሆን በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ ምክንያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል፡፡»

በቤተ ክርስቲያን ወስጥ ብዙ የአገልግሎት ዕድሎች አሉ፡፡ መጸለይ፣ መመስከር፣ ትራክቶችን ማሰራጨት፣ መዘመር፣ ማስተማር፣ መጠበክ እና ሌሎችን ወደ ቤተ ክረስቲያን መወሰድ ጥቂቶች ናቸው፡ በታማኝነት ቤተ ክርስቲያን መከታተልዎ እን● እግዚአብሔርን የሚያስደስትና ሌሎችንም የሚያበረታታ ነው፡፡

ዕብ 10፡25 «አንዳንዶች ማድረጉን እንዲተወት መሰብሰባችንን አንተው ይልቁንም ቀኑ እየተቃረበ መምጣቱን ስታዩ እርስ በርሳችን እንበረታታ፡፡»

**የሚከተሉትን ይስሩ**

አቶ ተስፋሁን በቤቱ ሆኖ መጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ስለሚችል ቤተ ክርስቲያን መሄድ አያስፈልገኝም ብሎ ያምናል፡፡ በአመለካከቱ የተሳሳተ መሆኑን እንዲረዳ በምን መልኩ ሊያስረዳት ይችላሉ? የተሻለ መልስ በሆነው ምክር ላይ ያስምሩበት፡፡

- 
- አያስፈልጉኝም ብሎ ቢያስብም እን● ጓደኞች እንዲሚያስፈልጉት ማስረዳት፡፡
- ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የመግናኘቱ ዓላማ ምን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ማስረዳት፡፡
- ሌሎች ክርስቲያኖች ገንዘብ ሲቸገራቸው ለረዳት እንደሚችሉ መንገር፡፡

# ክፍል 4

## በቤተ ክርስቲያን ላይ እየሆነ ያለዉ ምንድን ነው?

### የሁለት ሺህ አመታት ተጋድሎ

ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ከመሰረታት ጀምሮ ሰይጣን ወጊያ እያካሄደባት ይገኛል፡፡ ቤተክርስቲያን ነፍሳትን ከሰይጣን ወሽትና ሸንገላ ለማዳን በወጊያ ላይ ናት፡፡

**ኤፌሶን** 6፡12 «ተጋድሎአችን ከስጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ዓለም ገዢዎች ፣
ከስልጣናት ከኃይላት እንዲሁም ከሰማያዊ ስፍራ ካሉ ክርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር
ነው፡፡»

1 ጴጥ 5፡8 «ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፣ ንቁም ጠላታችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሳ አንበሳ ወዲህ ወዲያ ይዞራል»፡፡

### የሰይጣን ስልት እና መሳሪያዎች

ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን ለማሸነፍና ክርስቲያኖችን ከክርስቶስ ለመለየት ይጥራል፡፡ ዋና ዋና ስልቶቹ ስደት፣ ማታለልና ፈተና ናቸው፡

ክርስቲያኖችን ለማደል እና ለማክደድ ሰዎችን ይጠቀማል፡፡ የሐሰት አስተማሪዎችን ወደ ቤተ ክርስተያን ይልካል፡፡ ደካማ እና ኃይል የሌላቸው እንዲሆኑ በኃጢአት ይፈትናቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን እንዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል፡፡

## የቤተ ክርስቲያን ስልት እና መሳሪያዎች

የእኛ መከላከያ የሰራዊት አለቃ ከሆነው ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተጣብቆ መኖር ነው፡፡ ዋና ዋና መሳሪያዎቻችን ጸሎት፣ እምነት፣ እና የእግዚአብሔር ቃል ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን ማሸነፍ እንድንችል ብርታትና ኃይል ይሰጠናል፡፡

**ኤፌሶን** 6፡10፡11 «በተረፈ በጌታና ብርቱ በሆነው ኃይሉ ጠንክሩ፡፡ የዲያቢሎስን የተንኮል ስራ መደምሰስ ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔር ሙሉ የጦር እቃ ልበሱ፡፡»

## የቤተ ክርስቲያን ድል

በዘመናት ሁሉ ሰደት ቤተ ክርስቲያንን እንድትጠነክር እንድታድግ አደርጓል፡፡ ከኃጢአት እና ከሐሰት ትምህርቶች ያደናት ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ የመሳቃቀት ሚዛበልን ይልካል፡፡ አሁን መከራ ሊደርስብዎ ይችላል፤ ነገር ግን ጦርነቱ በቅርብ ጊዜ ይጠናቀቃል፡፡ ሰይጣን ይሸነፋል ቤተክርስቲያንም ለዘላለም ከክርስቶስ ጋር ትነግሳለች፡፡

**ማቴዎስ** 16፡18 «ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ፣ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም፡፡»

ሮሜ 8፡37 «በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን፡፡»

## በዚህ ሁሉ የእርስዎ ድርሻ

በዚህ ጦርነት ወስጥ እያንዳንዱ ክርስቲያን ወታደር ነው፡፡

2 **ጢሞ** 2፡3 «እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ በጎ ወታደር ከእኛ ጋር መከራን ተቀበል፡፡»

**ራዕይ** 2፡10 «ሊደርስብህ ያለውን መከራ አትፍራ እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሁን እኔም የህይወትህ አክሊል እሰጥሃለሁ፡፡»

| **የሚከተለውን ይስሩ** |
|---|
| 1 እያንዳንዱ ክርስቲያን እየተካሄደ ባለው መንፈሳዊ ውጊያ ወስጥ ያለ ወታደር ነው፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ክርስቲያን የ ………………….አለማ ነው፡፡ |
| 2 ክርስቲያን የሆነ ሰዉ ሰይጣንንና ወሸቱን ማሸነፍ የሚችለዉ የእዉነት ሰይፍ የሆነውን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .በመጠቀም ነው፡፡ |

## ይህን ኮርስ በማጠናቀቅዎ እንኳን ደስ አለዎ!

አሁን የክፍለ ትምህርት 6ን ጥያቄዎች በዚህ መፅሐፍ መጨረሻ ላይ ከሰሩ በኋላ አጠቃላይ መልሶችዎን በአቅራቢያዎ ለማገኘዉ ጽህፈት ቤታችን ይላኩልን፡፡

*ይህን ኮርስ በማጥናትዎ እንደተደሰቱ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ሌሎች ኮርሶቻችንም በመውሰድ እግዚአብሔር ለሕይወትዎ ያለውን ዕቅድ የበለጠ እንዲረዱ ይበርቱ እንላለን፡፡*

<u>እግዚአብሔር ይባርክዎ!</u>

# <u>የትምህርቶች መከለሻ ጥያቄዎች</u>

*መመሪያዎች*

*ግልፅ አድርገው ይፃፉ!*

ስም.................................................................................................

ፖ. ሳ .ቁ.........................................................................................

የመኖሪያ ቤት አድራሻ.........................................................................

የሚኖሩበት ከተማ...............................................................................

ስቴት/ክፍለ ግዛት............................የፖስታ/የመኖሪያ አካባቢ ኮድ...............

አገር...............................................................................................

የኢሜይል አድራሻ...............................................................................

የሕይወት ዓበይት ጥያቄዎችን አጠናቀው ሰርቲፊኬት ለማግኘት ከዚህ ቀጥሎ የሚገኙትን ጥያቄዎች በሙሉ ይመልሱ

መልስ የሰጡባቸውን ገጾች፣ የጓደኞችዎን ስምና አድራሻ ከያዘው ገፅ ጋር በጥንቃቄ ለይተው በማውጣት በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የግሎባል ዩኒቨርሲቲ ጽሕፈት ቤት ይላኩ።

*አሁን ከትምህርት 1-6 ላሉት ትምህርቶች የመከለሻ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተዘጋጅተዋል።*

*<u>የቻሉትን ያህል ለሁሉም ጥያቄዎች መልሳቸውን ይስጡ።</u>*

## ትምህርት 1

1. በትምህርት 1 ውስጥ ይህን ይሰሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ። ☐ አዎ ☐ አልሰራሁም

2. ስለ ሰው አፈጣጠርና ስለ ዓለም እውነትን የምንማርበት ብቸኛው ማገድ
............................................................
ነው፡፡
3. እግዚአብሔር ሰውንና ዓለምን የፈጠረው
ለ..................................................................... ነው፡፡
4. በሽታና ሞት ወደ ዓለም የመጡበት ምክንያት
.......................................................
5. በሐጢያታችን ምክንያት ሊመጣብን የነበረው ቅጣት የተወገደልን በ
............................................................
ነው፡፡

## ትምህርት 2

1. በትምህርት 2 ወስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ፡፡ ☐አዎ ☐አልሰራሁም
2. ስለ እግዚአብሔር እውነቱን ማወቅ ያለብኝ እርሱ
የእኔ...........................................
እና............................................................
ስለሆነ ነው፡፡
3. እግዚአብሔር በቃሉ ስለራሱ ከተናገረው ነገር ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም
ከግልዎ..............................................................
ሰለ እርሱ ማወቅ ይችላሉ፡፡
4. እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ነው፡፡ ሁሉን ያወቃል እንዲሁም .......................... ሚድረግ ይችላል፡፡
5. ለእርሱ ስላለዎ አምልኮ እግዚአብሔር እውነተኛና ታማኝ እንዲሆኑለት ይፈልጋል እንዲሁም
ስለ.............................................................
እንዲያመልግሉት ይፈልጋል፡፡

## ትምህርት 3

1. በትምህርት 3 ወስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ፡፡ ☐አዎ ☐አልሰራሁም
2. እኔና እርስዎ የተወለድነው የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆንና የእርሱን
መልክ.............................................................ነ
ው፡፡
3. ሰው ስለሆንኩ በጎወን ከክፉ ለይቼ ማወቅ፣ ወበትን ማድነቡ፣ ማሰብ ፣እግዚአብሔርን ማምለክና ጠቃሚ ነገሮችን መስራት እችላለሁ፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩት በወስጡ..........................መኖሩን ነው፡፡
4. ክፉ ነገሮችን የሚደርግና የስጋየን ፍላጎት ብቻ ለሚርካት ብቻ መኖሬ በወስጤ ያለው የእግዚያብሔር መልክ ...................................................... መሆኑን ያሳያል፡፡
5. እግዚአብሔርን ለማስደሰት ባህሪየን እርሱ
........................................................... እና በወስጤ
የእርሱን መልክ.........................................................
መፍቀድ አለብኝ፡፡
6. አያሱስን አዳኜ አድርጌ ስቀበል የእግዚአብሔር ልጅ እሆናለሁ የእርሱ አምሳል በወስጤ ይመላሳል፡፡ ይህ መሆኑን እግዚአብሔር የሚያሳየኝ
በ.............................፣በ...............................
ምስክርነትና በ..............................አማካኝነትና ነው፡፡

## ትምህርት 4

1. በትምህርት 4 ወስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ፡፡ ☐አዎ ☐አልሰራሁም
2. ከሁሉ በላይ የሆነወን ፍላጎት ያሟላን ሰው የሚገልፁ ሐሳቦች ላይ ያስምሩ
ማርታ መንፈሳዊ ሕይወትን ከእግዚአብሔር ተቀብላለች
ዮናስ ከዕወርነት ተፈወሶአል

ቶማስ ብዙ ገንዘብ የሚያገኝበትን መንገድ አገኝቶአል
ከበደ እየሱስ ክርስቲስ አዳኙ እንዲሆን ጠየቀ

3.ትልቁ ኃጢያት የእዘአብሔር ዋና ትዕዛዝ የሆነውን...............................ነው ይኸውም እግዚአብሔርን ...............................ነው፡"

4. እያሱስ ክርስቶስ ያደነኝ ዘንድ ለመጠየቅ የተሻለው ጊዜ ...............................ነው፡"

5. የመጀመሪያውን ስፍራ ለ ...............................ከሰጠሁ የምለብሰውንና የምበላውን እግዚአብሔር እንደሚሰጠኝ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡

# ትምህርት 5

1.በትምህርት 5 ወስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ፡፡ ☐አዎ ☐አልሰራሁም

2.የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሰው በሚሞትበት ጊዜ መንፈሱ ወደ ......................ይሄዳል፡"

3.እያሱስ ወደ ምድር ተመልሶ ሲመጣ የእርሱ የሆኑት ሁሉ እንደ ......................የሆነ አካል ይሰጣቸዋል፡፡

4. ምንግስተ ሰሚዩ እግዚአብሔር ለ......................ሁሉ ያዘጋጀው ስፍራ ነው፡፡ ሲዖል ደግሞ እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለ......................ያዘጋጀው ነው፡፡

5. ያለብኝን ......................ለእግዚአብሔር ከተናገርከና ......................አዳኜ አድርጌ ከተቀበልኩ የመንግስተሰሚዩን መንገድ መርጫለሁ፡፡

# ትምህርት 6

1. በትምህርት 6 ወስጥ ይህን ይስሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልሻለሁ በቃል የሚያዙ ጥቅሶችንም አጥንቻለሁ፡፡ ☐አዎ ☐አልሰራሁም

2. የእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑ ሰዎች......................N መሪያቸው አድርገው የሚከተሉ ናቸው፡፡

3. እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን አራት ዋና ዋና ነገሮችን ታደርጋለች፡፡ የሚከተሉትን ሐሳቦች በመሙላት እነዚህን ነገሮች ግለፅ፡

እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ......................ታመልካለች፣ ስለእያሱስ ......................ትናገራለች፣ ለምዕመናን ......................ታስተምራለች፣ እንዲሁም ......................ለሆኑት እንክብካቤ ታደርጋለች፡፡

4. የእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑት ......................በሚደረግ እርስ በርስ በመንፈሳዊ ህይወታቸው ለማደግ ይረዳዳሉ፡፡

5. እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን የሚፀራት የድል ዓይነት የ......................ን ሙሉ በሙሉ መሸነፍ ያካትታል፡፡

## <u>አስተያየቶችና ጥያቄዎች</u>

**ምናልባት የግል አስተያየትዎን መግለፅ ይፈልጉ ይሆናል ያ ከሆነ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ፡፡**

1.ትምህርት 1ን ከመጀመርዎ በፊት የእግዚአብሔርን ዕቅድ ተረድተው እያሱስን አዳኝዎ አድርገው ተቀብለው ነበር? አዎ/አይ

2.ያልተቀበሉ ከነበሩ እነዚህን ትመህርቶች ከተማሩ በኋላ ተቀበሉ? አዎ/አይ

3.እስካሁን ካልተቀበሉት አሁን ሊቀበሉት ይፈልጋሉ? አዎ/አይ

4.የሚሄዱበት ቤተ ክርሲያን አለዎ? አዎ/አይ
ከሆነ የትኛዋ ቤተ ክርስቲያን?

5.በአካባቢዎ የሚገኝ የቤተ ክርስቲያን አድራሻ ማገኘት ይፈልጋሉ? አዎ/አይ

6.እነዚህ ተምህርቶች ስለ እግዚአብሔር ብዙ እውነቶችን አካትተዋል አሁን በህይወትዎ ከሁሉ በላይ የረዳዎት የትኛ ነው?

